# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 239 ሚያዝያ 29 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# ከ11 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የአፈር ማዳበሪያ ለአርሶ አደሩ እየተሰራጨ ነው

## - ከ15 ሺህ በላይ ትራክተሮች የእርሻ አገልግሎት እየሰጡ ነው

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- ለ2016/17 ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ከ19 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የአፈር ማዳበሪያ ተገዝቶ ከ11 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የሚሆነው ለአርሶ አደሩ እየተሰራጨ ይገኛል ሲል ግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ ግብርናውን ለማዘመን በተሰራው ሥራ ከ15 ሺህ በላይ ትራክተሮች በግብርና ሥራ ላይ መሳተፋቸውም ተገልጿል፡፡

የግብርና ሚኒስቴር የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ስራ አስፈፃሚ አቶ ከበደ ላቀው ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ለ2016/17 የበልግና የመኸር ወቅት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ከ19 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የአፈር ማዳበሪያ ተገዝቶ ከ11 ሚሊዮን

ከ11 ሚሊዮን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# በስሱን የሚጠብቁ የሥራ ዕድል ተጠቃሚዎች

**አስቴር ኤልያስ**

**ዜና ሐተታ**

ቦታው ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ነው፤ የተለያየ የእጽዋት አይነትንም በውስጡ ይዟል፡፡ እርስ በእርሱ የተያያዘ የዛፍ አይነት በመሆኑ ወደ ውስጥ ለመዝለቅ ግራና ቀኝ ያለውን ቅርንጫፍ ከፍና ዝቅ እያደረጉ መሔድን ይጠይቃል፡፡ አልፎ አልፎ ደግሞ የተመነጠረ ገላጣ ቦታ የሚያጋጥም ሲሆን፣ እርሱም ቢሆን በንብ ቀፎ ተሞልቷል፡፡ ይህ ቦታ የሚገኘው በአዳማ ከተማ፣ በሉጎ ክፍለ ከተማ፣ በድሬ ነጋ ወረዳ፣ በደካ አዲ ቀበሌ ውስጥ ነው፡፡

አካባቢው በጸሐይ ንዳድ የተንገፈገፈውን ሰው የማቀዝቀዝ ኃይል አለው፡፡ የቅመማቅመም ዝርያዎችንም በውስጡ ስለያዘ የአካባቢው መዓዛ ስሜትን ያድሳል፡፡ እንደ በሶብላ፣ ጤና አዳም፣ አሪቲ፣ እና መሰል ተክሎች ገና በመብቀል ላይ ያሉ ቢሆኑም ደስ የሚል መዓዛ ማመንጨት በመጀመራቸው ስፍራውን ለቆ ለመሔድ አያስመኝም፡፡

በዚሁ በደካ አዲ ቀበሌ ውስጥ በሚገኘው ጫካ፤ በንብ ማነቡ ስራ ተደራጅተው በአካባቢው የተከሉትን

በስሱን የሚጠብቁ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ-ሀዲስ አብርሀ









# ዩኒቨርሲቲው የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓቱን እያዘመነ ነው

## - የሬጅስትራር አገልግሎቱ ወደኤሌክትሮኒክስ ሥርዓት ተሸጋግሯል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአገልግሎት አሰጣጡን ለማዘመን እየሰራ መሆኑን አስታወቀ፡፡ የዩኒቨርሲቲው የሬጅስትራር አገልግሎት ሙሉ ለሙሉ ወደኤሌክትሮኒክስ ሥርዓት መሸጋገሩም ተገልጿል፡፡

ዩኒቨርሲቲው የአገልግሎት... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ከሰበታ ከተማ ገቢ ወንዝ የሚወስደው የአስፓልት መንገድ ጥገና እየተደረገለት ነው

ገጽ 4




# ማህበሩ በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት የአባላቱን ቁጥር 20 ሚሊዮን ለማድረስ እየሠራ ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ የአባላቶቹን ቁጥር ከስድስት ሚሊዮን ወደ 20 ሚሊዮን ከፍ ለማድረግ እየሰራ መሆኑን አስታወቀ፡፡

የማህበሩ ፕሬዚዳንትና የአለም አቀፍ ቀይ ጨረቃ ማህበር የቦርድ አባል አቶ አበራ ቶላ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ማህበሩ በአሁን ወቅት ትኩረት ሰጥቶ እየሰራባቸው ካሉ ስራዎች አንዱ የአባላትንና የበጎ ፍቃደኞችን ቁጥር ማሳደግ ነው፤ በዚህም በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት የአባላቱን ቁጥር ከስድስት ሚሊዮን ወደ 20 ሚሊዮን ከፍ ለማድረግ እየሰራ ነው፡፡

እንደ አቶ አበራ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ ካላት 120 ሚሊዮን ህዝብ ውስጥ 80 ሚሊዮኑን የሚይዘው ወጣቱ ነው፡ ፡ በሀገሪቱ ያለው የወጣት ብዛት ሲታይ የአባላት ቁጥር እጅጉን አነስተኛ ነው፡፡ ማህበሩ ሀገራዊ ድርጅት ከመሆኑ አንጻር ሁሉም ወጣት የማህበሩ አባል እንዲሆን እቅድ በማዘጋጀትና በጀት በመመደብ እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው፡፡

ከዚህ ቀደም ማህበሩ ለዜጎች ግንዛቤ በመፍጠር የአባላት ቁጥሩን ለማሳደግ በትኩረት አልሰራበትም ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ አሁን ባሉት የአባላት ቁጥር



አቶ አበራ ቶላ

በኢትዮጵያ በየወቅቱ የሚከሰቱ ሰው ሰራሽና ተፈጥሯአዊ ችግሮችን ምላሽ ለመስጠት ማህበሩ አዳጋች መሆኑን አመልክተዋል፡፡

ለዚህም ማህበሩ በአሁን ወቅት ከማዕከል እስከ ክልል ባሉት ቅርንጫፎቹ በዳይሬክቶሬት ደረጃ አዲስ መዋቅር በመፍጠር ለሁሉም የኮታ ክፍፍል ያደገረ ሲሆን፤ የሚመለመሉ አባላትም የሚያስፈልጋቸውን ስልጠና እንዲወስዱና ስለ ሰብዓዊነት እንዲያውቁ እንደሚደረግ ፕሬዝዳንቱ ተናግረዋል፡፡

እንዲሁም አዲስ የኮሙንኬሽንና የሚዲያ ቡድኖችን በማዋቀር የአባላትን መረጃዎች በዲጅታል የመመዝገብ ተግባር እየተከናወነ መሆኑን የገለጹት አቶ አበራ፤ ወጣቱ በጎ ፍቃደኝነትን፣ መስጠትንና ደግነትን እንዲማር ለማድረግ ማህበሩ ቆርጦ መነሳቱን ተናግረዋል፡፡

እንደ አቶ አበራ አባባል፤ ግጭት፣ ድርቅ፣ የዜጎች መፈናቀልና ሞት ባይኖር ማህበሩ በልማት መስኮች ህዝብን በማሳተፍ ግንባር ቀደም ድርጅት በመሆን የሀገርን እድገት ሊያግዝ የሚችል ነው፡፡ ነገር ግን አሁን ላይ ይህንን ማድረግ አልቻለም፤ የሚያገኘውን ድጋፍ በተለያዩ አከባቢዎች ለሚፈጠሩ ችግሮች እንዲውሉ እያደረገ ነው፡፡

የዜጎችን ሰብዓዊ መብት ለመጠበቅና የሚያስፈልጋቸውን ቁሳቁስ በራሳቸው መግዛት እንዲችሉ ጥሬ ገንዘብ እየሰጠ መሆኑንም አቶ አበራ ተናግረዋል፡፡

እንደሀገር የሚታየውን የመድሀኒት እጥረት ለመቅረፍ ማህበሩ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች በሚገኙ ፋርማሲዎቹ መድሀኒቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ እያቀረበ እንደሚገኝ የጠቆሙት ፕሬዝዳንቱ፤ ሆኖም ተጨማሪ ሥራዎችን ለመስራት የውጭ ምንዛሬ እጥረት እንቅፋት እንደሆነበት አስረድተዋል፡፡

# የዩኒቨርሲቲ መውጫ ፈተና ከሰኔ 14 እስከ 21 ይሰጣል

## - 250 ሺህ የሚደርሱ ተማሪዎች ይፈተናሉ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የዩኒቨርሲቲ መውጫ ፈተና ከሰኔ 14 እስከ 21 ቀን 2016 ዓ.ም እንደሚሰጥ ትምህርት ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ ፈተናውን 250 ሺህ ለሚደርሱ ተማሪዎች ለመስጠት ዝግጅት መደረጉንም ገልጿል፡፡

በሚኒስቴሩ የአካዳሚክ ጉዳዮች መሪ ሥራ አስፈጻሚ ኤባ ሚጀና (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የዩኒቨርሲቲ መውጫ ፈተና ተማሪዎች ትምህርታቸውን አጠናቀው ሲወጡ ሊኖራቸው የሚገባውን እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ለመለካት የሚሰጥ ነው፡፡

የሚወጡ ጥያቄዎችም የየትምህርት ክፍሎች ምሩቃን እንዲኖራቸው የሚጠበቀውን እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት መሠረት አድርገው የሚዘጋጁ ናቸው፡፡

ሚኒስቴሩ ፈተናውን ለመስጠት አስፈላጊውን ዝግጅት ማጠናቀቁን ጠቅሰው፤ ፈተናው ተዘጋጅቶ እንዲገመገም ተደርጓል ብለዋል፡፡

ዶክተር ኤባ እንደገለጹት፤ ተፈታኝ ተማሪዎች መረጃም በመሰብሰብ ላይ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ከዚህ በፊት በኤክስኤል ሲቀበሉ ነበር፤ አሁን ላይ ግን የሚያጋጥሙ ስህተቶችን ለማረም እንዲቻል የተፈታኞች መረጃ አንላይን ላይ እንዲቀመጥ እየተሠራ ነው፡፡

ፈተናውን 250 ሺህ ለሚደርሱ ተማሪዎች ለመስጠት ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ጠቅሰው፤ ከግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ፈተናውን የሚወስዱ ተማሪዎች



ኤባ ሚጀና (ዶ/ር)

ዝርዝር በትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን ተረጋግጦ ነው ወደ ሚኒስቴሩ የሚላከው ብለዋል፡፡

በግል ተመዝግበው ፈተናውን በድጋሚ የሚወስዱ ተማሪዎች ምዝገባም በቀጣይነት የሚከናወን በመሆኑ አሁን ላይ ትክክለኛ ቁጥሩን ማስቀመጥ ያስቸግራል ብለዋል፡፡

ዩኒቨርሲቲዎች ተማሪዎችን ለፈተና ዝግጁ እንዲሆኑ ከማድረግ ጀምሮ አስፈላጊ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን ማጠናቀቃቸውን ገልጸው፤ በመብራት መቆራረጥ ምክንያት ፈተናው ላይ እክል እንዳያጋጥም በጄኔሬተር ለመስጠት ዝግጅት አድርገዋል ሲሉም ገልጸዋል፡፡

ፈተናው ላይ ሞባይል ይዞ የሚመጣና መታወቂያ ሳይዝ የሚመጣ ተማሪ ፈተናውን መውሰድ እንደማይችል ጠቅሰው፤ ባለፈው ጊዜ 114 የሚሆኑ ተማሪዎች ተንቀሳቃሽ ስልክ ይዘው በመግባታቸው ውጤታቸው እንዲሰረዝ ተደርጓል፤ በመሆኑም ተማሪዎች ይህን አውቀው ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባቸዋል ብለዋል፡፡ በቀጣይ ጊዜያት ፈተናው በካሜራና በጣት አሻራ ታግዞ እንዲሰጥ እቅድ መኖሩንም ጨምረው ገልጸዋል፡፡

የካቲት ላይ በተሰጠው ፈተና የአንድ ዩኒቨርሲቲ መምህር ወደ ሌላ ዩኒቨርሲቲ ሄደው ምልከታ እንዲያከናውኑ መደረጉን አስታውሰው፤ በቀጣይ በሚሰጠው ፈተና የአንድ ተቋም መምህራን ወደ ሌላ ተቋም ሄደው ፈተና እንዲሰጡ ለማድረግ እየተሠራ ነው ሲሉም ገልጸዋል፡፡

በመጀመሪያው የመውጫ ፈተና ከተፈታኞች 40 በመቶው ፈተናውን ማለፋቸውን አስታውሰው፤ ተፈታኞች የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡ በዩኒቨርሲቲዎች በኩል የተለያዩ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

በቀጣይ ጊዜያት እያንዳንዱ ዩኒቨርሲቲ ምን ያህል ተማሪዎችን እንዳስፈተነና ምን ያህል ውጤት እንዳስመዘገበ የሚያሳይ መረጃ ይፋ እንደሚደረግም ጨምረው ገልጸዋል፡፡

# ድጋፉ በጃፓን እና በኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል ያለውን ወዳጅነት ይበልጥ ያጠናክራል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የጃፓን መንግሥት በሲዳማ ክልል በደራ ኦትልቾ ወረዳ ለሚገኘው ተፈሪ ኬላ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ያደረገው የማስፋፊያ ግንባታ ድጋፍ በጃፓንና በኢትዮጵያ ህዝቦች መካከል ያለውን ወዳጅነት ይበልጥ እንደሚያጠናክር ተገለጸ፡፡

ድጋፉ ሰሞኑን ሲደረግ በኢትዮጵያ የጃፓን አምባሳደር ሺባታ ሂሮኖሪ እንደገለጹት፤ የተደረገው የድጋፉ ስምምነት በጃፓን እና በኢትዮጵያ ህዝቦች መካከል ያለውን ወዳጅነት የበለጠ ለማጠናከር ይረዳል፡፡ ድጋፉ ለትምህርት ቤቱ አራት የመማሪያ ክፍሎችን ከነሙሉ እቃው አካቶ የያዘ አንድ ህንጻ ለመገንባት የሚረዳ ነው። ግንባታው ሲጠናቀቅም ከ200 በላይ አዳዲስ ተማሪዎችን በትምህርት ቤቱ እንዲማሩ ያስችላቸዋል።

አጠቃላይ ለፕሮጀክቱ እስከ 70 ሺህ የአሜሪካን ዶላር ድጋፍ እንደሚደረግ ያነሱት አምባሳደሩ፤ የጃፓን መንግሥት በተለያዩ ዘርፎች ከኢትዮጵያ ጋር በጋራ እየሰራ መሆኑንና ትኩረት ከተሰጠባቸው ዘርፎች መካከልም የትምህርት ዘርፍ አንዱ እንደሆነ ተናግረዋል።

ለሕፃናት መሰረታዊ ትምህርት መስጠት ለሀገር ብሩህ ተስፋ መሆኑን ጠቁመው፤ ፕሮጀክቱ ወደትክክለኛ ትግበራ እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

አምባሳደር ሺባታ ሂሮኖሪ ትምህርት ቤቱ በፕሮጀክቱ ትግበራው ወቅት ከኤምባሲው ጋር ጥሩ ግንኙነት እንደሚኖረው እና ፕሮጀክቱን በፍጥነት በማጠናቀቅ ህፃናቱ አዲሱን የትምህርት ቤት ህንጻ በአፋጣኝ እንዲጠቀሙበት እንደሚደረግ አመላክተዋል።

የፌዴሬሽን ምክር ቤት የማንነት አስተዳደር ወሰንና የሰላም ግንባታ ዳይሬክተር ጴጥሮስ ወልደሰንበት በበኩላቸው፤ የቀድሞ ተፈሪ ኬላ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ መሆናቸውንና ለስራ ወደስፍራው በሄዱበት ወቅት ትምህርት ቤቱ እንደነበረ መመልከታቸውን አስታውሰው፤ እንዲሻሻል ፕሮጀክት አዘጋጅተው ተቀባይነት እንዳገኘ ተናግረዋል፡፡

ልጆች የአስተዳደግ ሁኔታቸው ምንም ይሁን ምን ጥራት ያለው ትምህርት እንዲያገኙ ሁሉም አካል ሳይታክት መትጋት እንዳለበት የገለጹት አቶ ጴጥሮስ፤ የማስፋፊያ ግንባታው በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ እንደሚጠናቀቅ አመላክተዋል፡፡

ይህ የድጋፍ ስምምነት በኢትዮጵያ የትምህርት ተደራሽነትን እና ጥራትን ለማሳደግ በሚደረገው ጥረት አስደሳች ምዕራፍ መጀመሩን እንደሚያሳይና ፕሮጀክቱ መሠረተ ልማቶችን ከማቅረብ ባለፈ ተማሪዎችን ወደ ሙሉ አቅማቸው እንዲደርሱ የሚያበረታታ እና ምቹ የትምህርት አካባቢ ለመፍጠር እንደሚረዳ አቶ ጴጥሮስ ጠቁመዋል።

ጃፓን በኢትዮጵያ የትምህርት እና በተለያዩ የልማት ዘርፎች ላይ ድጋፍ ስታደርግ እንደነበር ያነሱት አቶ ጴጥሮስ ለትምህርት ቤቱ ድጋፍ እንዲደረግ ጥያቄ ባቀረቡበት ወቅት የጃፓን ኤምባሲ ላደረገው ድጋፍ እና አጋርነት ምስጋና አቅርበዋል፡፡



መሳይ ሀይሉ(ዶ/ር)

# ውሃ ወለድ በሽታዎች እንዳይከሰቱ የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራውን በቅንጅት መሥራት ይገባል

## - በ297 ወረዳዎች የኮሌራ በሽታን መቆጣጠር ተችሏል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- የክረምት ወራትን ተከትሎ ውሃ ወለድ በሽታዎች እንዳይከሰቱ የመከላከልና የመቆጣጠር ስራው በቅንጅት ሊሰራ እንደሚገባ የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት አስታወቀ፡፡ በ297 ወረዳዎች የኮሌራ በሽታን መቆጣጠር መቻሉም ተመላክቷል፡፡

የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር መሳይ ሀይሉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የክረምት ወራትን ተከትሎ ውሃ ወለድ በሽታዎች እንዳይከሰቱ የመከላከልና የመቆጣጠር ስራው ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል፡፡

ኮሌራ፣ ወባና ኩፍኝ በሽታዎች በሀገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች ከተከሰተ ጊዜ ጀምሮ የመቆጣጠርና የመከላከል ስራ እየተሰራ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

የኮሌራና ሌሎች ውሃ ወለድ በሽታዎችን ከመቆጣጠር አንጻር የህክምናና ሌሎች ቁሳቁሶች ቶሎ እንዲደርሱ ክትትል የማድረግ፣ ህብረተሰቡን የማስገንዘብ እና የመጸዳጃ ቤት ሽፋንና አጠቃቀም ዝቅተኛ በሆነባቸው አካባቢዎች ላይ የማሻሻል ስራ መሰራቱን ገልጸዋል፡፡

በድርቅ ምክንያት የንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋን ዝቅተኛ በሆነባቸው አካባቢዎችም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር አቅርቦትን የማሻሻል ስራ በመሰራቱ ኮሌራ በተከሰተባቸው በአብዛኛዎቹ አካባቢዎች መቆጠጠር የተቻለ ሲሆን፤ በምሥራቅ ኦሮሚያ፣ በሶማሌና አፋር ክልሎች የተወሰኑ ወረዳዎች ላይ የበሽታው ስርጭት ያለ በመሆኑ ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር እየተሰራ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ኮሌራ ከተከሰተ ጊዜ ጀምሮ በተሰራው የመከላከል ስራ በ297 ወረዳዎች ላይ ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር መቻሉን ገልጸው፤ በሽታው በባህሪው ተላላፊ በመሆኑ የንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋንን በማስፋፋት እና ውሃን አክሞ በመጠጣት ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር ይገባል ብለዋል፡፡

የወባ በሽታን ለመከላከል ለማህበረሰቡ ተደራሽ የተደረገውን አጎበር በአግባቡ እንዲጠቀም ግንዛቤ የማስጨበጥ እና የወባ ምልክት የታየባቸውን ሰዎች በመለየት ህክምና እንዲያገኙ የማድረግ ስራ መሰራቱን ገልጸዋል፡፡

ለወባ መራቢያ ምቹ የሆኑና ውሃ ያቆሩ ቦታዎችን በህብረተሰብ ተሳትፎ የማጽዳት፣ የኬሚካል ርጭት፣ ለወባ ምርመራ የሚያገለግሉ የህክምና ቁሳቁሶችን የማሰራጨት ስራ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራቱ ተጠናክሮ ቀጥሏል ብለዋል፡፡

እንደ ዶክተር መሳይ ገለጻ፣ በምዕራብ ኦሮሚያ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ በቤኒሻንጉል እና በምእራብ አማራ፣ ክልሎች ላይ የወባ በሽታ የጨመረበት ሁኔታ በመኖሩ የመከላከል ስራው በቅንጅት እየተሰራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የኩፍኝ በሽታን የመደበኛ ክትባት ማጠናከር እና ተጨማሪ የክትባት ዘመቻ በመደረጉ ከ320 በላይ ወረዳዎች ላይ መቆጣጠር መቻሉን አስረድተዋል፡፡ መደበኛ ክትባትን የማጠናከርና የታመሙ ህጻናት ህክምና እንዲያገኙ በስፋት ይሰራል ብለዋል፡፡

ተላላፊ እና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ህብረተሰቡን ማንቃት ወሳኝ ነው ያሉት ዶክተር መሳይ፤ የግልና የአካባቢ ንጽህናን፣ የምግብና መጠጥ ውሃ ንጽህናን መጠበቅ እንደ ኮሌራ ያሉ ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ጠቀሜታው የጎላ ነው ብለዋል።

የክረምት ወራትን ተከትሎ ውሃ ወለድ በሽታዎች እንዳይከሰቱ የመከላከልና የመቆጣጠር ስራው ተጠናክሮ እንዲቀጥልና ህብረተሰቡም ጥንቃቄ እንዲያደርግ አሳስበዋል፡፡



አሳምነው ተሾመ (ዶ/ር)

# የወቅቱ ዝናብ

## በበልግ ወቅት ለሚዘሩ አዝርዕቶችና ቋሚ ተክሎች ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው

### - በአንዳንድ አካባቢዎች ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊኖር እንደሚችልም ተጠቁሟል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የወቅቱ ዝናብ በበልግ ወቅት ለሚዘሩ አዝርዕቶችና ቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎትን ከማሟላት አኳያ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው የኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩት አስታወቀ። በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊከሰት ስለሚችል ህብረተሰቡ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበትም ኢንስቲትዩቱ አሳስቧል፡፡

በኢንስቲትዩቱ የሜትሮሎጂ ትንበያና ቅድመ ማስጠንቀቂያ ምርምር ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አሳምነው ተሾመ (ዶ/ር) ለኢፕድ እንደገለጹት፤ የወቅቱ የዝናብ መጠንና ስርጭት በበልግ ወቅት ለሚዘሩ አዝርዕቶችና ቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎትን በማሟላት ምርታማነትን ከማሳደጉም ባሻገር በሀገሪቱ ለሚገኙ 12 የሚደርሱ ተፋሰሶች የውሃ ይዞታቸው እንዲጨምር በማድረግ ለቀጣይ የመኸር ዝግጅት ለማከናወን ያግዛል፡፡

ኢንስቲትዩቱ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ወቅቶች ከመጀመራቸው አንድ ወር ቀደም ብሎ የሚኖረውን የዝናብ መጠንና ስርጭት የትንበያ ውጤት ይፋ እንደሚያደርግ ገልጸው፤ በልግ ዋነኛና ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠንና ስርጭት ይኖረዋል ብለዋል፡፡

እንደ አሳምነው (ዶ/ር) ገለጻ፤ በኢትዮጵያ የክረምት፣ የበጋና የበልግ ወቅቶች እያንዳንዳቸው የአራት ወራት ጊዜን የያዙ ሲሆን የአሁኑ የበልግ ወቅት ከየካቲት እስከ ግንቦት ያሉትን ወራት ያቅፋል፡፡ በአሁን ወቅትም በተለያዩ የሀገሪቱ አከባቢዎች መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠንና ስርጭት እየተስተናገደ ይገኛል፡፡

በደቡብ አጋማሽ፣ ሲዳማ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በሱማሌ ክልል፣ በጉጂና በቦረና አካባቢዎች በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸው ነው፡፡ ምስራቅና ደቡብ ትግራይ፣ ሰሜንና ደቡብ የወሎ ዞኖች፣ የአማራና የኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ሀረር፣ ድሬዳዋና አዲስ አበባን የበልግ ወቅት ሁለተኛ ዝናብ የሚያገኙበት ጊዜ ነው፡፡

በበልግ ወቅት ከፍተኛ የዝናብ መጠን እየተመዘገበ እንደሚገኝ አንስተው፣ ለአብነትም 60 ከሚደርሱ የሜትሮሎጂ ጣብያዎች በተሰበሰበ መረጃ በ24 ሰዓት ውስጥ አዲስ አበባ፣ አዳማ፣ ቢሾፍቱ፣ ሀረር፣ ድሬዳዋ፣ ከፊል ሶማሌና የኦሮሚያ ክልል የሀገሪቱ አከባቢዎች ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ማስተናገዳቸውን ጠቁመዋል፡፡

በተለይም በሆሳዕና፣ በባቲ፣ በድሬዳዋ፣ በአዲስ አበባና በሌሎችም የነበረው ከባድ የዝናብ መጠን አሉታዊ ተጽዕኖ ነበረው ያሉት አሳምነው (ዶ/ር)፤ እንዲሁም በተወሰኑ አካባቢዎችም በግብርና የስራ እንቅስቃሴዎች ላይ ተጽዕኖውን ማሳረፉን ተናግረዋል፡፡

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ የሚኖረው የዝናብ መጠንና ስርጭት የበልግ ወቅት የግብርና ስራዎችን ለማከናወን ከፍተኛ ጠቄሜታ ይኖረዋል፡፡ እንዲሁም ለአርብቶና አርሶ አደሩ እንስሳት የመጠጥ ውሃና የመኖ አቅርቦትን ከማሻሻል አኳያ አስተዋጽኦ አለው፡፡

በሚቀጥሉት የበልግ ወራት በተለይም ለበልግ ዝናብ መፈጠር አመቺ የአየር ሁኔታዎች ይበልጥ ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ የትንበያ ምንጮች እንደሚያመለክቱ ጠቁመው፣ በዚህም ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠንና ስርጭት ይኖራል ብለዋል፡፡

የአዋሽ ተፋሰስ፣ ስምጥ ሰለቆ፣ የዋቢ ሸበሌ፣ የኦሞ ተፋሰሶችና ሌሎችም በበልግና በክረምት ወቅት ከሚኖረው ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ጋር ተያይዞ ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊከሰትባቸው የሚችሉ አካባቢዎች በመሆናቸው ከወዲሁ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

# በክልሉ የማዕድን ምርት አሠራር ሕጋዊ መልክ እንዲኖረው ሥርዓት እየተዘረጋ ነው

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በትግራይ ክልል የማዕድን ምርት አሰራር ሕጋዊ መልክ እንዲኖረው ሥርዓት እየተዘረጋ መሆኑን የክልሉ የመሬትና ማዕድን ቢሮ አስታወቀ፡፡

የክልሉ መሬትና ማዕድን ቢሮ ኃላፊ አቶ ፍስሃ ግርማይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳሉት፤ በክልሉ ከጦርነቱ በኋላ ሕገ ወጥ ማዕድን የማውጣት እና የመሸጥ ስራዎች በመበራከታቸው ይህንን ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በተለያዩ አካባቢዎች በጉልበት እና ሕጋዊ በማስመሰል ያለአግባብ ማዕድን የመዝረፍ ሁኔታዎች እንዳሉ ጠቅሰው፤ይሁን እንጂ ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር በክልሉ ያለው ፖለቲካዊ አለመረጋጋት በተወሰነ ደረጃ ዕንቅፋት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ችግሩን ከህዝብ ጋር በመነጋገር ወደ ሥርዓት ለማስገባት ጥረቶች በማድረግ ጅማሮዎች መኖራቸውንም ኃላፊው ጠቅሰዋል፡፡

የወርቅ ማዕድን በኮንትሮባንድ ይሸጥ እንደነበር ጠቅሰው፤ይህንን ለመቅረፍ እና ለመለወጥ በተቻለ መጠን ከህዝብ እና ከወጣቶች ጋር በመወያየት ሕጋዊ ለማድረግ እየተሰራ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

ኃላፊው እንዳሉት፤ ሕጉን ተከትለው እየሰሩ የሚገኙት ቀደም ሲል ቦታ ወስደው ሲያለሙ የነበሩ ናቸው፡፡ በመሆኑም በጦርነቱ ምክንያት የባከኑ ዓመታትን ግምት ውስጥ በማስገባት ወደ ስራ እንዲገቡ መደረጉን ገልጸዋል፡፡ ሌሎች አዳዲስ ወጣቶችም ማዕድን ማውጣት ስራ ላይ እንዲሰማሩ ተደርጓል፡፡

በመሆኑም በርካታ ወጣቶች በሕጋዊ መንገድ ለመስራት በዘርፉ መሰማራታቸውን ጠቅሰው፤በተቃራኒው ደግሞ ቁጥራቸው የማይናቅ ወጣቶችም በሕገ ወጥ መንገድ እንደተሰማሩ ጠቁመዋል፡፡ ቀደም ሲል ከነበረው አካሄድ አሁን ላይ የቁጥጥር ስርዓቱን መልክ እያስያዝነው ነው ሲሉም ተናግረዋል፡፡



አቶ ፍስሃ ግርማይ

የወርቅ ማዕድን ከሚገኙባቸው አካባቢዎች መካከል በማእከላዊ ዞን ወርዒ፣ሽረ፣ምስራቃዊ ዞን ገጠራማ አካባቢ ተጠቃሽ መሆናቸውን ጠቁመው፤ ይህንን የሚሰሩት የህብረት ስራ ማህበራት አቅማቸው ዝቅተኛ በመሆኑ አቅም ለመፍጠር እየተሰራ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

በመሆኑም የማዕድን ምርት አሰራር ስርዓቱ እንዲጠበቅ እና በሕጋዊ መንገድ እንዲከናወን በትኩረት እየተሰራ መሆኑን ገልጸው፤በክልሉ የሚገኝ ህዝብ እና ወጣት ለማዕድን ሃብት ትኩረት በመስጠት ከባለ ድርሻ አካላት ጋር መረጃዎችን በመለዋወጥ ጥበቃ ማድረግ ይኖርበታል ሲሉ አሳስበዋል፡፡



ሰቃ ፏፏቴ

# በኦሮሚያ በቱሪዝም ዘርፍ ከ34 ቢሊዮን ብር በላይ ተንቀሳቅሷል

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል ባለፉት ዘጠኝ ወራት በቱሪዝም ዘርፍ ከ34 ቢሊዮን ብር በላይ መንቀሳቀሱን የክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ፡፡ ክልሉ በዘጠኝ ወራት ውስጥ ከ11 ሚሊዮን በላይ በሆኑ የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች እንዲሁም ከ204 ሺህ በላይ የውጭ ሀገር ቱሪስቶች ተጎብኝቷል፡፡

በኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የእቅድና በጀት ዳይሬክተር አላና ተሾመ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ ቢሮው በ2016 ዓ.ም የዘጠኝ ወራት ጊዜ ውስጥ ከ34 ቢሊዮን ብር በላይ ማስገኘት ችሏል፡፡

እንደ አቶ አላና ገለጻ፤ ከሀገር ውስጥ የቱሪስት ፍሰት የሚገኝ ገቢ እስከ ዘጠነኛ ወር 33 ቢሊዮን 075 ሚሊዮን በክልሉ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ አስተዋጽኦ ማድረግ ችሏል። ከውጭ ሀገር ቱሪስት ፍሰትም እስከ ዘጠነኛ ወር ድረስ አንድ ቢሊዮን 229 ሚሊዮን 400 ሺህ ብር ሊገኝ ችሏል፡፡ በጠቅላላውም ከ34 ቢሊዮን ብር በላይ በክልሉ ኢኮኖሚ ውስጥ ተንቀሳቅሷል፡፡

አቶ አላና እንደገለጹት፤ ክልሉ በዘጠኝ ወራት ውስጥ ከ11 ሚሊዮን 59 ሺህ 99 የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች እንዲሁም ከ204 ሺህ 900 የውጭ ሀገር ቱሪስቶች ተጎብኝቷል፡፡

የክልሉን የቱሪዝም ሀብቶች የተለያዩ ሥልቶች በመጠቀም ማስተዋወቅ የሴክተሩን ራዕይ ለማሳካት ጥረቶች ተደርገዋል ያሉት አቶ አላና፤ በዚህም መሠረት የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ በመጠቀም፤ የተለያዩ ህትመቶች በማዘጋጀት የገበያ ፕሮሞሽን መረጃዎች ተደራጅተዋል ብለዋል፡፡

መረጃዎቹን በማሰራጨት የቱሪዝም ገበያ ትንተና ማካሄድ፣ የተለያዩ ኢግዝብሽኖችን ማዘጋጀትና ለዕይታ የማብቃት፤ የኢንቨስትመንት ዕድሎችና ጎብኚዎችን የመሳብ ሥራና የመሳሰሉት ሥራዎች በስፋት ሲሰሩ ቆይተዋል ሲሉም ገልጸዋል፡፡

በማህበራዊ ሚዲያዎች የተሰራጩ የቱሪስት መረጃዎችን በሚመለከት አቶ አላና እንደገለጹት፤ እስከ ዘጠነኛ ወር ስምንት ሺህ ታቅዶ ስድስት ሺህ (75 በመቶ) ያህሉ ሊከናወን ችሏል፡፡

የተዘጋጁና የተሰራጩ የተለያዩ የህትመት ውጤቶች እስከ ዘጠነኛ ወር ሶስት ታቅዶ ሶስት ወይም 100 በመቶ ተከናውኗል ሲሉም ተናግረዋል፡፡

በክልሉ ከፍተኛ የቱሪስት ፍሰት ከሚታይባቸው ሁነቶች መካከል ዋንኛዎቹ የኢሬቻና መሠል ባህላዊና ትውፊታዊ በዓላት እንዲሁም የቁልቢ ገብርኤልና የደብረሊባኖስ ገዳማት የንግስ አከባበርን የመሳሰሉ የሃይማኖት በዓላት ይጠቀሳሉ።

# ከሰበታ ከተማ ጊቤ ወንዝ የሚወስደው የአስፓልት መንገድ ጥገና እየተደረገለት ነው

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- ከሰበታ ከተማ ጊቤ ወንዝ ድረስ የሚወስደው የአስፓልት መንገድ ጥገና እየተደረገለት እንደሚገኝ የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር አስታወቀ፡፡ መንገዱን በአንድ ዓመት ጊዜ ለማጠናቀቅ እየተሰራ ሲሆን የአንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር በጀት መያዙም ተመላክቷል፡፡

በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ተጠሪ መሃንዲስ ኢንጂነር ፍፁም ባዩ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳሉት፤ የመንገድ ስራው ከሰበታ ቆራ እና ከቆራ ጊቤ የሚዘረጋና ደረጃውን የጠበቀ የአስፖልት የጥገና መንገድ ነው።

ከሰበታ ቆራ ድረስ የሚወስደው 64 ኪሎ ሜትር የሚሸፍን ሲሆን፤መነሻውን ሰበታ ከተማ ዲማ በማድረግ ቆራ ከተማ መዳረሻውን እንደሚያደርግ ጠቅሰው፤የመንገድ ጥገናው ክፍል የሆነው የቆራ ጊቤ ወንዝ ፕሮጀክት 93 ኪሎ ሜትር እንደሚሸፍን ተናግረዋል፡፡

ፕሮጀክቱ ከአዲስ አበባ 157 ኪሎ ሜትር ርቀት የሚሸፍን ሲሆን፤ከተጀመረ ከሁለት ዓመት በላይ ማስቆጠሩን ገልጸው፤መንገዱ ቆራ ከተማ መውጫ ላይ ጀምሮ ጊቤ ወንዝ ድልድይ ላይ እንደሚያበቃ ጠቁመዋል፡፡

የጥገና ስራው ሀገር በቀል ቴክስ ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከኤምሲጂ ኮንስትራክሽን ጋር በጥምረት እየተሰራ ሲሆን፤ የማማከር እና የቁጥጥር ስራው ኤስጂ ኮንሰልቲንግ ኢንጂነርስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እያከናወነው እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

መንገዱ ተሰርቶ ሲያልቅ ዘርፈ ብዙ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች እንዳሉት በመጥቀስ፤ከደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍል የሚገኘውን የቡና ምርት በፍጥነት ወደ መሃል ሀገር እና ወደ ውጭ ገበያ ለመላክ እንደሚያስችል ገልጸዋል፡፡

መንገዱ የኦሮሚያ ልዩ ዞን፣ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን እና ጉራጌ ዞን የሚያገናኝ ሲሆን፤ከቱሪዝም ጋር ተያይዞ ወደ ጅማ አባጅፋር ቤተ መንግሥት ለመጓዝ እንዲሁም ወደ ጊቤ ወንዝ ብሔራዊ ፓርክ ለመድረስ ትልቅ ፋይዳ እንዳለው አስረድተዋል፡፡

በተጨማሪም በአካባቢው በስፋት የሚመረተው የጤፍ፣ ቆጮ ሽምብራ፣አቦካዶ እና የበቆሎ ምርት በቀላሉ ወደ ማዕከል ገበያ ለማድረስ የሚረዳ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

ቀድሞ የነበረው መንገድ በአገልግሎት ዘመኑ ረዥም ጊዜ ያስቆጠረ ሲሆን በቀን እስከ አራት ሺ ተሽከርካሪ ሲያስተናግድ በመቆየቱ ለከባድ ብልሽት መጋለጡን ጠቁመዋል፡፡ በዚህም ምክንያት በርካታ የተሽከርካሪ አደጋ ይከሰት እንደነበር አስታውሰዋል፡፡



ፕሮጀክቱ በሁት ተከፍሎ እየተከናወነ እንደሚገኝ የገለፁት ኢንጅነር ፍፁም፤ ቀላል ብልሽት ያለው አስፓልት በመደረብ እና ከባድ ጉዳት የደረሰበት ደግሞ የመልሶ ግንባታ ስራ እየተሰራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የፕሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅ ኢንጅነር ሀብቶም ግደይ በበኩላቸው፤ፕሮጀክቱ እስከ አሁን ድረስ 18 ኪሎ ሜትር አስፓልት መስራቱን በመጥቀስ፤ ስራው በፍጥነት እንዳይጠናቀቅ የነዳጅ እጥረት እና የኮንስትራክሽን ግብአት ዋጋ መናር ጫና መፍጠራቸውን አመልክተዋል፡፡

በመሆኑም ፕሮጀክቱን በፍጥነት ለማጠናቀቅ ተጨማሪ የስራ ሰዓት በመጠቀም እንዲሁም ተጨማሪ ማሽነሪዎችን በማስገባት በአንድ ዓመት ለማጠናቀቅ ርብርብ እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

# ዩኒቨርሲቲው...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

የዩኒቨርሲቲው ሬጅስትራር ዋና ዳይሬክተር አደይ ፈለቀ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዩኒቨርሲቲው በቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ነው፡፡ የሬጅስትራር አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓቱንም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያዘመነ ይገኛል፡፡

በዚህ ሂደት ሙሉ ለሙሉ ወረቀት ተኮር ከሆነው ሥርዓት ወደኤሌክትሮኒክ ሥርዓት ሽግግር ተደርጓል ብለዋል፡፡

በዚህም በሬጅስትራሩ አሰራር ሥርዓት ተማሪዎች በቅድሚያ በተዘረጋላቸው የኦንላይን መንገድ አስፈላጊውን ቅድመ ሁኔታ በማሟላት እንዲያመለክቱ እንደሚደረግ ጠቁመዋል፡፡

ከጤና ሚኒስቴር ተመድበው ለሚመጡ ተማሪዎች ብቻ ባለድርሻ አካላቱ የትምህርት እና የጤና ሚኒስቴር ስር በመሆናቸው ሂደቱ እንደሚለይ ገልጸዋል፡፡

ተማሪዎች ከምዝገባ ጀምሮ የመግቢያ ፈተናቸውንም በኦንላይን በመውሰድ ውጤት እዚያው በፍጥነት እንዲያውቁ እንደሚደረግ ያነሱት አደይ (ዶ/ር)፤ 99 በመቶው የተማሪዎች የማመልከቻ ሥርዓት በኦንላይን እንደሚከናወን ተናግረዋል፡፡

የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች በትምህርት ክፍል መረጣ ወቅት፣ ተማሪዎች በሚያመለክቱበት ጊዜና በሌሎችም ሂደቶች በአሰራር ሥርዓቱ ላይም ሆነ በተለያዩ ሁኔታዎች የሚነሱ ቅሬታዎች ሲኖሩ ሬጅስትራሩ እንደ አስፈላጊነቱ ፈጣን ምላሾችን እየሰጠ እንደሆነ ዳይሬክተሯ ጠቅሰዋል፡፡

እንደ እርሳቸው ገለጻ፤ ሬጅስትራሩ የድህረ ምረቃ፣ የቅድመ ምርቃ እና የሶስተኛ ዲግሪ ተማሪዎች ለትምህርት ወደ ዩኒቨርሲቲው በሚመጡበት ወቅት አስፈላጊውን ሂደት አሟልተው እንዲመጡ በማድረግ ወደመማር ማስተማር ሥርዓቱ እንዲቀላቀሉ እያደረገ ነው፡፡

ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲው በሚያደርጉት ቆይታ የሚጠበቅባቸውን በማሟላት ትምህርታቸውን አጠናቀው ለምረቃ ብቁ በሚሆኑበት ወቅት ከዩኒቨርሲቲው ሴኔት ጋር በመማከር ምርቃታቸውን የማጽደቅ ተግባር እንደሚያከናውንም ገልጸዋል፡፡

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ራስ ገዝ መሆን በተለያዩ ዘርፎች የሚፈጥራቸው ምቹ ሁኔታዎች እንዳሉ ዶክተር አደይ ተናግረዋል፡፡ የዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ መሆን አሠራራቸውን ለማዘመንና ራዕያቸውን እንዲያሳኩ ትልቅ ሚና እንደሚጫወት ጠቁመዋል፡፡

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ራስ ገዝ ከሆነ በኋላ በርካታ መሻሻሎችን እያመጣ መሆኑንም በማሳያነት አንስተዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት ከተማሪዎች ቅበላ እና ከክፍያ ስርዓት ጋር ተያይዞ እየተቀየሰ ያለውን ፖሊሲና መመሪያን መሰረት በማድረግ በሚቀጥሉት ዓመታት የትምህርት ክፍያውን ጨምሮ በርካታ የሚሻሻሉ ጉዳዮች ይኖራሉ ሲሉም አክለዋል፡፡

# ከ11 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የአፈር ማዳበሪያ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ኩንታል በላይ የሚሆነው የአፈር ማዳበሪያ ለአርሶ አደሩ እየተሰራጨ ይገኛል፡፡

በ2016/17 ምርት ዘመን ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ 19 ነጥብ አራት ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ግዥ የተፈፀመ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ ከ11 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ወደ ሀገር ውስጥ ተጓጉዞ ለአርሶ አደሩ እየተሰራጨ ነው ብለዋል፡፡

በ2016/17 የምርት ዘመን አገልግሎት ላይ እንዲውል ከተገዛው 19 ነጥብ አራት ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ውስጥ 25 በመቶ የሚሆነው ለበጋ መስኖ ስንዴ ልማት የዋለ ሲሆን 20 በመቶ የሚሆነው ለበልግ እንደሚውልና 55 በመቶ የሚሆነው ደግሞ ለመኸር የሚውል ይሆናል ሲሉ አብራርተዋል፡፡

በ2014/15 የምርት ዘመን የተከሰተው የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት ችግር በ2016/17 እንዳይከሰት የግዥ ስርአቱን የማሻሻል፤ አስቀድሞ የመግዛት፣ ስርጭቱን የመከታተልና የመቆጣጠር ስራ እየተሰራ ነው ያሉት አቶ ከበደ፤ ይህ በመደረጉ በቂ የሆነ የአፈር ማዳበሪያ ለበልግ እንዲቀርብ አስችሏል ብለዋል፡፡

ከዚህ በፊት ከሚገዛበት በዘንድሮው ዓመት ቀደም ብሎ አፈር ማዳበሪያው እንዲገዛ መደረጉ ጊዜና ጉልበትን ከመቆጠቡ ባለፈ አርሶ አደሩ ተረጋግቶ ግብዓቱን በሚፈልገው ሰዓት በቀላሉ እንዲያገኝ ይረደዋል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

አቶ ከበደ እንደገለጹት፤ ወደ ሀገር ወስጥ የተጓጓዘው ከ11 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የአፈር ማዳበሪያ ከማዕከላዊ መጋዘን ወደ ክልሎች ገበሬ ማህበራት ተዘዋውሮ ለአርሶ አደሩ እየተሰራጨ ይገኛል፤ ስርጭቱ ላይ ህገ ወጥ አሰራሮች እንዳይኖሩም የሚከታተልና የሚቆጣጠር ግብረ ኃይል ተቋቁሙ እየተሰራ ነው፤ ስርጭቱ ላይም የጎላ ችግር የለም፡፡

የሀገሪቱን የግብርና ዘርፍ በማዘመን ምርትና ምታማነትን ለማሳደግ እየተሰራ ባለው ስራ የግብርና መካናይዜሽንና የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን የመጠቀም ስራ እየተሰራ እንደሆነም አቶ ከበደ አብራርተዋል፡፡

የግብርና መካናይዜሽና የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም እየተሰራ ባለው ስራ በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት፤ በበልግና በመኸር እርሻ ላይ ከ15 ሺህ በላይ ትራክተሮች ጥቅም ላይ ውለዋል፤ ለቀጣይ የመኸር እርሻ ቁጥራቸውን በማሳደግ ጥቅም ላይ የማዋል ስራ እየተሰራ ነው ሲሉም ገልጸዋል፡፡

የግብርና መካናይዜሽን መሳያዎችን ማለትም ትራክተሮች፤ ኮባይነሮችና የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን ከቀረጥ ነፃ በሆነ መንገድ በማህበራትና በአርሶ አደሮች እንዲገቡ እየተደረገ ነው ያሉት ስራ አስፈፃሚው ይህ አሰራርም ቁጥራቸውን እያሳደገው ነው ብለዋል፡፡

ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር የግብዓት አቅርቦትን የማሳደግና በወቅቱ የማሰራጨት ስራ በትኩረት እየተሰራበት ይገኛል ሲሉም አመላክተዋል፡፡

# በስሱን የሚጠብቁ የሥራ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

የጓሮ አትክልት ሲንከባከቡ ያገኘናቸው ወይዘሮ ብዙወርቅ ዘገየ የማኅበራቸው ስም አብዮት፣ አበበችና ጓደኞቻቸው የሚል እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ በማኅበሩ ስም የተደራጁት አስር ሲሆኑ፣ ሰባት ሴቶችና ሶስት ወንዶች ናቸው፡፡

እርሳቸው እንደሚሉት፤ ከተደራጁ በኋላ ወደስራ ከመግባታቸው በፊት በንብ ማነብ ዙሪያ የተዘጋጀላቸውን ስልጠና ወስደዋል፡፡ የስራ እድል ተፈጥሮላቸው ወደ ስራ ከገቡ ገና ወራት ያህል ያስቆጠሩት የማኅበሩ አባላት፤ የመጀመሪያ ስራቸው ያደረጉት ጫካውን ለቀፎና ለመተላለፊያ ይሆን ዘንድ በመመንጠር ምቹ ማድረግ ነው፡፡ ቦታውን ማጽዳት ዋጋ አስከፍሏቸዋል፡፡ ለንቦች ጠንቅ የሆነው ‘ጥቁሮ’ የሚባል የአበባ አይነት ንቦችን እንዳይገድላቸው ለማጥፋት ጥረዋል፡፡

የሰነቁት ትልቅ ተስፋ ከፊታቸው ስላለ አሁን እያደረጉ ባለው እንቅስቃሴ ደስተኛ መሆናቸውን ያመለክታሉ፡፡ ወይዘሮ ብዙወርቅ የሚባክን ጊዜ የላቸውም፤እዛው ቀፎው አካባቢ ቀን ቀን አረፍ የሚሉባቸው ማረፊያ ብጤ አበጃጅተዋል፡፡ ንቡ አካባቢውን ለቆ እንዳይሰደድ በአካባቢው የተለያዩ የጓሮ አትክልቶችን በመትከል ይንከባከባሉ፡፡ በተለይም ለንቦች መስሕብ የሆኑ እንደ ድንብላል፣ በሶብላ፣ አሪቲ፣ የመጥበሻ ቅጠል፣ ጤና አዳምና ሌሎች ድንቅ መዓዛ ያላቸውን ተክሎች በመትከል ንቡ በመዓዛው ተስቦ ተረጋግቶ እንዲቀመጥ ይታትራሉ፡፡

ውሏቸው በስራ የተሞላ ነው፤ ይቆፍራሉ፤ ያርማሉ፤ አካባቢውን ለንቦች ምቹ ያደርጋሉ፡፡ ንቦቹን ማጣት አይፈልጉም፡፡ ተስፋቸው እነርሱ ላይ ነው፡፡ ለአንድ ቀፎ የሚሆን ንብ የሚገዛው እስከ አንድ ሺ 200 ብር ድረስ ነው፤ እሱንም ቢሆን የሚገዙት ከሌላ ቦታ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ማኅበራቸው ያለው 25 ቀፎዎች ሲሆን፣ እነርሱ በማር ይሞሉ ዘንድ ሳይታክቱ ይሰራሉ፡፡ ነገን ተስፋ አድርገው ማር ሰሪዋን ታታሪዋን ንብ ይንከባከባሉ፡፡ ምንም እንኳ እስካሁን ከቀፏቸው ማር ቆርጠው ባያውቁም ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን ይህ እንደሚሆን ጥርጥር የላቸውም፡፡ በመታገስ ጣፋጭ ፍሬ እንደሚበላ ስለሚያውቁ በትዕግስት እየተጠባበቁ ይገኛሉ፡፡

አብዮት፣ አበበች፣ ገነትና ጓደኞቻቸው የንብ እርባታ የሚባል ማኅበር በዚያው በጫካ ውስጥ የሚገኝ ሌላኛው የስራ እድል የተፈጠረለት ማኅበር ነው፡፡ የዚህ ማኅበር አንዷ አባል የሆኑት ወይዘሮ ገነት በቀለ እንደሚሉት፤ ተደራጅተው ስራ የጀመሩት አስር ሆነው ነው፡፡ ሁለት ወንድና ስምንት ሴቶች ናቸው፡፡ ወደስራ የገቡት በዚህ ዓመት ጥቅምት ወር ላይ ሲሆን፣ ንቦችን ቤት ለእንቦሳ ያሏቸውም በዚያው በጥቅምት ወር ውስጥ ነው፡፡

ወይዘሮዋ፣ ከዛ በፊት ይሰሩ የነበረው የተገኘውን አይነት ስራ ሲሆን፣ የቀን ስራም ሆነ ንግድም ይሞካከሩ እንደነበር ያረዳሉ፡፡ ይህ የንብ ማነቡ ስራ ጥሩ ነው። ለሴት ይከብዳል እያሉ ቢያወሩ እኛ ደስተኞች ሆነን እየሰራን ነው ይላሉ። ነገር ግን የውሃ ችግር እንዳለባቸው አልሸሸጉም፡፡ እሱ ከተስተካካለ ችግር እንደሌለና የስራቸውን ውጤት ለማየት እንደሚናፍቁ ያመለክታሉ፡፡

በአሁኑ ሰዓት ካሏቸው ቀፎዎች ውስጥ ወደ ሃያ ቀፎ ውስጥ ንብ አስገብተዋል፡፡ ንቦችን የሚያመጡት ከሌላ ቦታ በመሆኑ የአየር ሁኔታ ሲምታታባቸው የመረጋጋት አቅም አይኖራቸውም፡፡ ከዚህ የተነሳ እየወጡ ለመጥፋት ይሞክራሉ፡፡ ነገር ግን እንደዚያ እንዳይሆን ንቦችን ማርኮ የሚያስቀራቸው ነገር ላይ ትኩረት አድርገው እየሰሩ ይገኛሉ፡፡

በሌላው በማኅበር ከተደራጁ መካከል ወጣት ሰሜን አዲሱ ትጠቀሳለች፤ ወጣቷ በዚያ ጫካ ውስጥ ከወዲህ ወዲያ የምትለው በባዶ እግሯ ነው፡፡ የዘሩትን በቆሎ፣ ፓፓያ፣ ሙዝና ሌሎች ተክሎችን ትንከባከባለች፡፡ እነዚህ ሁሉ የሚውሉት ለንቦቹ ምግብነት እንደሆነም ትናገራለች፡፡ ምክንያቱም የተለያዩ ዝርያዎችን የተከልናቸው ንቦቹ አበባ እንዲቀስሙ በማሰብ ነው ስትልም ታስረዳለች፡፡

መንግሥት ካደራጀን በኋላ መሬት ሰጥቶናል፡፡ የተወሰነ የንብ ቀፎም ሰጥቶናል፡፡ የራሳችን ቀፎ 30 ሲሆን፣ መንግሥት የሰጠን ደግሞ 20 ቀፎ ነው፡፡ በአሁኑ ሰዓት ስራው ላይ የምንገኘው በተነቃቃ ስሜት ነው ትላለች፡፡ ንብ የማነቡን ተግባር ከጀመሩ ገና አራት ወር ሊሆናቸው እንደሆነም ታመለክታለች፡፡

ወጣቷ ሰሜን፣እንደምትለው፤ ማኅበራቸው ወደስራ የገባው ሃያ ሺ ብር ይዞ ነው፡፡ እርሷ ባለችበት ማኅበር ውስጥ የታቀፉት ከዚህ በፊት ተምረው አጥጋቢ ውጤት ያልመጣላቸው ስራ አጥ ወጣቶች ናቸው፡፡ በአሁኑ ሰዓት ከተማውና ክፍለ ከተማው ባደረጉት ቀናነት ስራ መጀመር ችለዋል፡፡ በዚህም በጣም ደስተኞች ናቸው፡፡ የስራቸውን ውጤትም በትጋት በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ፡፡ ከፍሬው ለመቋደስ እንደሚችሉም ሙሉ እምነት አላቸው፡፡

በአሁኑ ወቅት እንደ ችግር የማነሳው ነገር ቢኖር ውሃ አለመኖር ነው የምትለዋ ወጣት፣ ስራ ስንሰራ ቆይተን ቢያንስ መታጠብ ብንችልና ለንቦቹ ውሃ ቢያስገቡልን ጥሩ ነበር ትላለች፡፡

የአዳማ ከተማ የስራ እድል ፈጠራ ጽህፈት ቤት ምክትል ኃላፊ አቶ ፋፋ ገርማማ በበኩላቸው፤ከተማው ለንብ አንቢዎች ማኅበር የሰጠው አካባቢ እንደ ቦታኒክ ጋርደን የከለለው ጭምር ነው ይላሉ፡፡ ብዙ እጽዋትም ያሉበት ስፍራ እንደመሆኑ አካባቢው ከንኪኪም ነጻ እንዲሆን መደረጉን ይናገራሉ፡፡ ቦታው አዳማ ከተማም ልክ እንደ ጅማና ሌላ አካባቢ ንብ በማነብ የማር ምርት መቁረጥ እንደሚቻል አንዱ ማሳያ ነው ይላሉ፡፡

እርሳቸው እንደሚሉት፤በዚህ ጫካ ውስጥ በ18 ማኅበር ተደራጅተው የሚገኙ 180 አባላት ናቸው፡፡ ወደ ሁለት ሺ 700 ቀፎ በመግባቱ ስራ ተጀምሯል፡፡ በመሆኑም ከግንቦት ወር ጀምሮ ማር ይቆረጣል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

በአካባቢው ያለውን የውሃ እጥረት ከከተማ አስተዳደሩ ጋር እና ከስራ እድል ፈጠራ ጽህፈት ቤት ጋር በመሆን በውሃና ፍሳሽ ግምቱ 300 ሺ ብር የሆነ ገንዘብ ወጪ ተደርጎ ስለተጠናቀቀ ከሰሞኑን የሚገባላቸው መሆኑን ኃላፊው ይጠቁማሉ፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሃይማኖታዊ እሴቶችን ማሰብና መተግበር የበዓላት ወቅት ትኩረቶቻችን ብቻ መሆን የለባቸውም!

የሰው ልጅ ሰብአዊ እሴቶችን ጠብቆ ለመጓዝ የሚያስችሉ የሞራል አስተምሮዎች ባለቤት ነው። እነዚህ እሴቶች በአብዛኛው የሃይማኖታዊ አስተምህሮዎች መሰረት ሆነው በስፋት የሚጠቀሱ ናቸው። የሰውን ልጅ የለት ተዕለት ሕይወት በመግራት ያላቸው አስተዋጽኦም መተኪያ የሌለው ነው።

እምነት ፣ተስፋ ፣ፍቅር ፣ሰላም ፣ ትህትና ፣ በጎነት ፣ቸርነት ፣ አስተዋይነት እና ይቅርባይነት ወዘተ የየትኛውም ሃይማኖት አስተምህሮ መሰረቶች ናቸው። ከእነዚህ መንፈሳዊ እሴቶች ውጪ ሃይማኖት እና ሃይማኖተኝነትን ፤ ሰው እና ሰብአዊ እሴቶችን ማሰብ የሚቻል አይደለም። የሰው ልጅ ፍጥረታዊ ህልውናም ለእነዚህ እሴቶች የተገዛ እንደሆነ ይታመናል።

ከዚህ የተነሳም የሰው ልጅ እንደ ግለሰብ ሆነ እንደ ማኅበረሰብ ህልውናውን እስጠብቆ ለማቆየት፤ እንደተቀበለው ሃይማኖታዊ አስተምህሮ ፤ለነዚህ መንፈሳዊ እሴቶች ራሱን አስገዝቶ ለመኖር የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል። በተሳካለት መጠን ትርጉም ያለው ሕይወት መኖር የሚያስችለውን እድል ይፈጥራል።

ሁኔታዎች በተለያዩ ገፊ ምክንያቶች ከአቅሙ በላይ ሲሆኑበት /እንደ ግለሰብም ሆነ ማኅበረሰብ/ ትርጉም አልባ ፣ የተዘበራረቀ ሕይወት ለመኖር ይገደዳል። በተለይም የእለት ተእለት ሕይወቱ በነዚህ መንፈሳዊ እሴቶች እየተገራ ካልሄደ ፣ አጠቃላይ የህይወት ጉዞው በብዙ ተግዳሮቶች የሚፈተን እና የተጎረባበጠ መሆኑ የማይቀር ነው።

ከዚህ የተነሳም መንፈሳዊ እሴቶችን ማሰብ እና ለእነርሱ የሚገዛ ህይወት ለመፍጠር የሚደረግ ጥረት ፣ ሃይማኖታዊ በአላት እና በአላትን ተከትሎ በሚደረጉ ሥርዓቶችን ተከትሎ ብቻ የሚከናወን አይደለም፣ ከዚህ ይልቅ እሴቶቹን የህይወት መርህ አድርጎ መውሰድ እና መተርጎምን የሚጠይቅ ነው።

እንደሌሎች ሃይማኖቶች ይህ አስተምህሮ በክርስትና ሃይማኖት ገዝፎ የሚስተዋል ነው። ሃይማኖቱ ከሁሉም በላይ ሰውን ሰው ላሰኙ መንፈሳዊ እሴቶች ከፍ ያለ ትኩረት የሚሰጥ ፣ እነዚህ እሴቶች የእለት ተእለት የህይወት መርህ አድርጎ መውሰድን የመኖር ትርጉም አልፋ እና ኦሜጋም አድርጎ በስፋት የሚሰብክ/የሚያስተምር ነው።

እንደ ግለሰብ ብቻ ሳይሆን እንደ ማኅበረሰብ ላለን የጋራ ሕይወት ስኬት እነዚህ እሴቶች ዋነኛ ጉልበት እንደሆኑ ከማስተማር ባለፈ ፣ እንደ ግለሰብ ብቻ ሳይሆን ዛሬ ላይ እንደሀገር ፈተና ከሆኑብን ችግሮቻችን ወጥተን ፣ተስፋ ያደረግናቸውን ነገዎቻችን ለመውረስ እነዚህ መንፈሳዊ እሴቶች መተኪያ የሌላቸው አቅሞቻችን እንደሆኑ አበክሮ ያስተምራል።

እነዚህ እሴቶች በአንድም ይሁን በሌላ ለሀገረ መንግሥት ምስረታችን ሆነ፣ ሀገረ መንግሥቱ ዘመናት እንዲሻገር፣ ከዚያም በላይ እንደ አንድ ትልቅ ማህበረሰብ /ሕዝብ ተጋምደን ዛሬ ላይ እንድንደርስ የነበራቸው አስተዋጽኦ ከፍ ያለ እንደሆነ ይታመናል። ነገ ላይ ተስፋ ለምናደርጋት የበለጸገች ኢትዮጵያም አቅሞች ስለመሆናቸው ለማሰብ የሚከብድ አይደለም።

ዛሬ ላይ እየተፈታተነን ላለው ፍቅር ማጣት ከዚህ የሚመነጭ ጥላቻ እና አለመደማመጥ ከዚህ የሚመነጭ የቋንቋ መደበላለቅ፣ እልኸኝነት ከዚህ የሚመነጭ ዳተኝነት፣ ራስ ወዳድነት ከዚህ የሚመነጭ ሕሊና አልባነት ፣ ስግብግብነት እና ነፍሰ ገዳይነት ልንወጣ የምንችለው በእለት ተእለት ሕይወታችን ለእነዚህ መንፈሳዊ እሴቶቻችን ስፍራ ስንሰጥ ብቻ ነው።

እነዚህም እሴቶች ሃይማኖታዊ በዓላት ፤ለማስታወስ ከዛም በላይ ለመኖር የሚደረጉ ጥረቶች የሚበረታቱ ቢሆኑም ፣ከሃይማኖት ቀናቱ ባለፈ ፣የእለት ተእለት የህይወት መርህ አድርጎ መውሰድ ከያንዳንዱ ምእመናን የሚጠበቅ ነው ።ይህን ማድረግ ስንችል ብቻ ነው እንደ ግለሰብም ሆነ እንደ ማህበረሰብ ያለን ሕይወት ትርጉም ያለው፤ ከትናንት የተሻለ ፣ ነገን ተስፋ ሊያደርግ የሚችለው።

ከዚያም በላይ ፣እንደሀገር ካለንበት የግጭት አዙሪት ወጥተን ያለንን የተፈጥሮ ሀብት አልምተን ፣ለራሳችንም ሆነ ለመጪው ትውልድ የተሻለች ሀገር የምንገነባው፤ ከአሮጌ ትርክቶች ወጥተን አዲስ የሀገር እና የሕዝብ ልዕልና የተላበሰ ትርክት መፍጠር የምንችለው!

አዲስ ዘመን
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል :- epa@press.et

ዋና አዘጋጅ
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው።በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## እውነተኛ የጀግኖች አርበኞች ልጆች እንሁን!

ወንድይራድ ሰይፈሚካኤል

ኢትዮጵያ ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ በተለያዩ ጊዜያት በርካታ ጀግኖችን ያፈራች ሀገር ናት። ወራሪ ኃይሎች የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት በመዳፈር በመዳፋቸው ስር ሊያስገቧት አስበው ብዙ ሞክረዋል። መሰል ተደጋጋሚ ሙከራዎችን ካደረጉት ወራሪዎች መካከል አውሮፓዊቷ ኢጣሊያ በግንባር ቀደምትነት ትጠቀሳለች። የፍራንቼስኮ ክሪስፒዋ ኢጣሊያ ዓድዋ ላይ የተከናነበችውን የሽንፈት ካባ በድል ለማካካስ በማሰብ በፋሺስቱ ቤኒቶ ሙሶሊኒ እየተመራች በ1928 ዓ.ም አሰቃቂ ወረራ በመፈፀም ለአምስት ዓመታት ያህል ኢትዮጵያን ቅን ተገዢዋ ለማድረግ ጥረት አድርጋም ነበር።

ይሁን እንጂ መቼውንም ቢሆን በሀገሩና በነፃነቱ የማይደራደረው የኢትዮጵያ ሕዝብ የፋሺስትን አገዛዝ «አሜን» ብሎ አልተቀበለውም። ይልቁንም ጨርቄን ማቄን ሳይል «ጥራኝ ዱሩ» ብሎ ለነፃነቱ መፋለም ጀመረ። የኢጣሊያ ወራሪ ኃይልም አንዲትም ቀን እንኳን እፎይ ብሎ ሳይቀመጥ ከአምስት ዓመታት እልህ አስጨራሽ ትግል በኋላ ሌላ የሽንፈት ማቅ ለብሶ ከኢትዮጵያ ምድር ተባረረ። ሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም፣ ከስደት የተመለሱት ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ በአዲስ አበባ፣ ታላቁ ቤተ መንግሥት ተገኝተው የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ሰቀሉ።

ታዲያ በዚህ አስገራሚና አኩሪ የመስዋዕትነት ጉዞ ውስጥ ኢትዮጵያውያን አርበኞች ያሳዩት ደማቅ የጀግንነት ታሪክ ምንጊዜም ቢሆን አይዘነጋም። ኢትዮጵያውያን አርበኞች በወራሪው የፋሺስት ጦር ላይ ድል የተቀዳጁት እጅግ መራራ ትግሎችን አድርገውና መስዋዕትነቶችን ከፍለው ነው። የየካቲት 12-15 የአዲስ አበባ፣ የሚያዝያ ሦስት የአመፀኛ ዋሻ እና የግንቦት 12 የደብረ ሊባኖስ አሰቃቂ ጭፍጨፋዎች የመስዋዕትነቶቹ ማሳያዎች ናቸው።

ይሁን እንጂ የፋሺስት ኢጣሊያ አሰቃቂ ጭፍጨፋዎች የኢትዮጵያውያንን የፀረ-ፋሺዝም ትግል ማስቆም አልቻሉም። ጀግኖቹ አርበኞች በቂ ስንቅና ትጥቅ ሳይቀርብላቸው ልጆቻቸውንና የትዳር አጋሮቻቸውን ጭምር በማሠለፍና በዘመኑ የነበረው ውስጣዊ ሽኩቻ ሳይበግራቸው፣ እግራቸውን ለጠጠር ደረታቸውን ለጦር ሰጥተው በከፍተኛ ፍቅርና ጀብዱ እናት ሀገራቸውን ከፋሺስቶች ባርነት ታድገዋል። ኢትዮጵያንም ብቸኛዋ ለቅኝ ገዥዎች ያልተንበረከከች አፍሪካዊት ሀገር በማድረግ ስሟን በደማቅ ቀለም አስፍረዋል።

ቀደም ባሉት ዘመናት ኢትዮጵያ በውጭ ጠላቶች ላይ ድሎችን በመቀዳጀት ረገድ ዓለም የሚደነቅባቸው አንፀባራቂ ታሪኮችን አስመዝግባለች። ጉራዕ፣ ጉንደት፣ ሰሃጢ፣ ዶጋሊ፣ ዓድዋ፣ ካራማራ እና የፀረ-ፋሺስት አርበኞች ድል የእነዚህ ታሪኮች ጥቂት ማሳያዎች ናቸው። እነዚህ ድሎች ኢትዮጵያውያን ለጋራ ዓላማ በጋራ ተሰልፈው ዓለምን ያስደነቀ ገድል መፈፀማቸውን ለመላው ዓለም ያሳዩባቸው አኩሪ ገድሎች ናቸው።

ይሁን እንጂ እነዚህ ድሎች ያስገኙት በረከትና የፈጠሩት እድል በሚገባ ተመንዝሮ ጥቅም ላይ አልዋለም። የእነዚህን ድሎች ትርጉሞችና በረከቶችን እያሰብን የኢትዮጵያን ያለፉትን ዓመታት (በተለይ 50 ዓመታት) ጉዞ ስንቃኝ «ለመሆኑ ኢትዮጵያ/ኢትዮጵያውያንና የጉንደት/ጉራዕ/ዓድዋ/ካራማራ/የፀረ-ፋሺስት አርበኞች(ሚያዝያ 27) ድሎች ይታወቃሉ?» ብለን ለመጠየቅ እንገደዳለን። ሀገሪቱ በረሃብ፣ በግጭት፣ በዘረኝነትና በጦርነት ጎዳናዎች ላይ ደጋግማ መመላለሷና ከድህነት ጋር ተቆራኝታ መዝለቋ እነዚህ ታላላቅ ድሎች ያስገኙላትን በረከቶች መዘንጋቷንና አለመጠቀሟን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል።

ዓለምን ያስደነቀው የጀግኖቹ ኢትዮጵያውያን አርበኞች ታሪካዊ ገድል ሲዘከር፣ የአሁኑ ትውልድ ዙሪያውን የከበቡትን ችግሮች እንዴት በድል መወጣት እንደሚችል ትምህርት መቅሰምና በጥልቀት ማሰብ ይኖርበታል። ሀገር ከችግር የምትላቀቀው በሁሉም ዜጎች ትብብር እንጂ በተናጠል እርምጃ አይደለም።

አርበኞች በፋሺስት ጦር ላይ ድል የተቀዳጁት በትብብር ባካሄዱት ትግል ነው። ከተባበሩና ከሁሉም ነገር በፊት ሀገርን ማስቀደም ከተቻለ የኢትዮጵያን አሁናዊ ችግሮች ድል ማድረግ እንደሚቻል ከአርበኞቹ የጋራ ትግልና ድል መማር ይቻላል። ኢትዮጵያውያን በችግሮቻቸው ላይ ድል ለመቀዳጀት በትብብር መስራታቸው አስገዳጅ ይሆናል። በትብብር ያልተሰራ ሥራ ዘላቂና አስተማማኝ ውጤት የማስገኘት እድሉ አነስተኛ ነው። ስለሆነም አቅምን አሰባስቦና ደምሮ በቅንጅት ለመሰለፍ ቁርጠኝነትና ዝግጁነት ሊኖር ይገባል።

**የኢትዮጵያን ችግሮች ለመፍታት የሚያስፈልገው ሌላው ግብዓት ጽናት ነው:: አርበኞችን ለድል ያበቃው ቁልፍ ምስጢር ፅናታቸውና ወኔያቸው ነበር**

ኢትዮጵያ የገጠሟትን ዘርፈ ብዙ ፈተናዎች ድል ለማድረግ ከግል ጥቅም ይልቅ ኢትዮጵያን ማስቀደም ይገባል። አርበኞች ለኢትዮጵያ ክብር ለመፋለም ሲወስኑ የግል ኑሯቸውን ትተው ነው። የሀገርን ችግር ለመፍታት ከግላዊ ዓላማና ስንቅ ይልቅ ሀገራዊ ዓላማ መያዝ ያስፈልጋል። ለሀገር ጥቅምና ኩራት የሚከፈል ዋጋ መራራ ቢሆንም ውጤቱ ግን ጣፋጭና የሚያኮራ ነው።

ኢትዮጵያን ከህመሟ ለመፈወስ በቅድሚያ ሀገርንና ሕዝብን መውደድና ማክበር ይገባል። የሀገርና የሕዝብ ፍቅር ያለው ግለሰብና ቡድን ሁልጊዜም ቢሆን ኃላፊነት ይሰማዋል። ኃላፊነቱን ለመወጣት ደግሞ ከሌሎች ጋር ስለመተባበር፣ በጥንቃቄና በፅናት ስለመራመድ ብሎም ስለማሸነፍ ያስባል፤ ይተጋል። አርበኞች ለሀገራቸው ክብር የተፋለሙት ሀገራቸውንና ወገናቸውን ስለወደዱና ስላከበሩ ነው።

የኢትዮጵያን ችግሮች ለመፍታት የሚያስፈልገው ሌላው ግብዓት ጽናት ነው። አርበኞችን ለድል ያበቃው ቁልፍ ምስጢር ፅናታቸውና ወኔያቸው ነበር። የጀግኖቹ ኢትዮጵያውያን ተጋድሎ ሲወሳ ለአምስት ዓመታት የተደረገ እልህ አስጨራሽ ትግል መሆኑን መዘንጋት አይገባም። ይህ መራር ትግል ፅናትን የሚፈታተን፤ መፈጠርን የሚያስጠላ፤ አባት፣ እናት፣ ወንድም፣ እህትና ሌሎች ወገኖች ሳይቀሩ በፋሺስቶች ጭካኔ የተጨፈጨፉበት፤ ሞት በየዕለቱ በርካቶችን ያጋዘበት፣ መንደሮች በየቀኑ በፋሺስቶች የጦር አውሮፕላኖችና መድፎች ሲወድሙ የሕፃናትና የእናቶች እሪታ ከዕልቂት ጋር የተሰማበት ነበር። ፊት ለፊት ከገጠመው ግዙፍ አውሮፓዊ ጠላት ጋር ከሚደረገው ትንቅንቅ ባልተናነሰ፣ በግለሰብ አመራሮች መካከል በሚፈጠር አለመግባባት ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰ ተስፋ አስቆራጭ አጋጣሚዎች የታዩበት፣ ስመጥር አዋጊ አርበኞች ለፋሺስቶች ባደሩ ባንዳዎች በሽምቅ የተገደሉበትና የፋሺስቶች ፕሮፓጋንዳ እየተነዛ መወላወል የተስተዋለባቸው ፈታኝ ሥቃዮች በጽናት የታለፉበት የትግል ጉዞም ነበር።

የኢትዮጵያ ችግሮችም እልህ አስጨራሽ ትግል፣ ጽናትንና ተስፋ አለመቁረጥን የሚጠይቁ ናቸው። አንዱ ችግር ሲፈታ ሌላ የችግር ምንጭ እንደሚፈልቅ አይተናል። እነዚህን ችግሮች ጠራርጎ ለማስወገድ ደግሞ ተስፋ አለመቁረጥ ያስፈልጋል። የሁሉንም ችግሮች ምንጭ ለማድረቅ የሚያስችል የጽናት ኃይል መታጠቅ እጅግ ያስፈልጋል።

ኢትዮጵያውያን አንዱን ችግር ከፈቱ በኋላ፣ ሌላ ችግር ሲፈጠር ተስፋ የሚቆርጡ ከሆነ ሁለ ገብ ድል አይገኝም። የዘላቂና አስተማማኝ ድል ባለቤት ለመሆን ችግሮች በየጊዜውና በየቦታው ሊፈጠሩ እንደሚችሉ ቀድሞ መጠበቅና መዘጋጀት እንዲሁም ሁሉንም ችግሮች ለመጋፈጥ በጽናት መቆም ይገባል። ኢትዮጵያ በሁሉም መስኮች አሸናፊ እንድትሆን የአሸናፊነት ወኔ ሊኖር ይገባል። ልብ ከደከመና ተነሳሽነት ከሌለ አሸናፊነት አይታሰብም።

ምክንያታዊ አስተሳሰብ ቦታ እንዲያገኝ መትጋት ያስፈልጋል። ምክንያታዊነት ማሰብን፣ ማሰላሰልን፣ ሚዛናዊ ዕይታንና መመርመርን የሚጠይቅ እንዲሁም «ምን?»፣ «እንዴት?»፣ «ለምን?»፣ «መቼ?»፣ «የት?» የሚሉትንና ሌሎች ተያያዥ መሠረታዊና አመክንዮን የተከተሉ ወሳኝ ጥያቄዎችን በማንሳት እውነትን ከሐሰት አብጠርጥሮ የማጥራት እሳቤን ይይዛል። ከአርበኞች ድል ተምሮ ኢትዮጵያን በክብር ለማሻገር «ለምን?» እና «እንዴት?» ብሎ ለመጠያየቅ፣ ለመከራከርና ለመወያየት የሚያስችል የሰለጠነ ባህል ማዳበር እጅግ አስፈላጊ ነው። ይህን ማድረግ ከቻልን «የጀግኖች አርበኞች ልጆች ነን» ብለን የማውራት ሞራል ይኖረናል።

# ነፃ ሃሳብ

# የኮሪደር ልማቱ እና አዲስ የሥራ ባህል

እስማኤል አረቦ

ኢትዮጵያ ለዘመናት ስትፈተንባቸው ከቆየችባቸው የልማት ማነቆዎች ውስጥ የፕሮጀክቶች መጓተት አንዱና ዋነኛው ነው። ሀገሪቱ በፕሮጀክቶች መጓተት የምትታወቅና በርካታ የሕዝብ ሀብትም ለኪሳራ ሲዳረግባት የቆየች ሀገር ነች።

ይህ ደግሞ ከዝቅተኛ የሥራ ባህልና ከፕሮጀክቶች የሥራ አመራር ክህሎት ማጣት ጋር የሚያያዝ ነው። በዋነኝነት የሥራ ባህላችን ዝቅተኛ መሆን የተጀመሩ ፕሮጀክቶች ዓመታት እንዲፈጁና እንደሀገር የኢኮኖሚ ኪሳራ እንዲደርስብን ምክንያት ሆኗል። በተለይም ከመሠረተ ልማት ግንባታ ጋር በተያያዘ ብዙ መገለጫዎች ያሉት ነው። በደካማ የሥራ ባህልና በፕሮጀክቶች የአመራር ጥበብ ማነስ የተነሳ ተጀምረው የተጓተቱና ጭራሹንም መጨረስ ያልቻልናቸው ፕሮጀክቶች ተቆጥረው የሚያልቁ አይደሉም።

ተጀምረው ከተረሱት ውስጥ የስኳር ፋብሪካዎች፤ የማዳበሪያ ፋብሪካ፤ የግብርና ማቀነባበሪያዎችና የመሳሰሉት እስካሁንም ተጀምረው የቀሩ ናቸው። በደካማ የሥራ ባህል የተነሳ በጾም በጸሎት የሚያልቁ ፕሮጀክቶችን ስናይ ደግሞ እንደሀገር የት እንደነበርን በቀላሉ መገንዘብ ያስችለናል። አብነት እንዲሆነን ጥቂቶቹን እንመልከት።

ቀደም ባለው ጊዜ አንድ ባለ 12 ወለል ህንጻ ለማጠናቀቅ እስከ 15 ዓመታት ይወስድ እንደነበረ የተደረጉ ጥናቶች ያመላክታሉ። ለአብነት መሃል ፒያሳ ላይ የሚገኘው በተለምዶ አራዳ ህንጻ ተብሎ የሚታወቀው ባለ 12 ወለል ህንጻ ከ15 ዓመታት በላይ ወስዷል። በደርግ ጊዜ ተጀምሮ በኢህአዴግ ዘመነ መንግሥት የተጠናቀቀ ዓመታትን የፈጀ ህንጻ ነው።

የመንገድ ፕሮጀክቶችም ቢሆኑ አንዱ መገለጫቸው ከተያዘላቸው ጊዜ በላይ መፍጀታቸው ነው። ለአብነትም ከአቡነ ጴጥሮስ እስከ አስኮ ያለው መንገድ በሁለት ዓመታት ውስጥ ይጠናቀቃል ተብሎ ከአምስት ዓመታት በላይ መውሰዱ የሚታወቅ ነው።

በተመሳሳይም የኮተቤ አራራት መንገድ በግንባታ መዘግየት ብዙዎችን ሲያማርር ቆይቷል። መንገዱ በሁለት ዓመታት ውስጥ ይጠናቀቃል ቢባልም ከሰባት ዓመታት በላይ በመዘግየቱ መንግሥትን ለበርካታ ወጪ ህብረተሰቡን ደግሞ ለቅሬታ ዳርጓል።

በተጨማሪም በ2009ዓ.ም የተጀመረውም የቃሊቲ ማሳለጫ በሁለት አመት ተኩል ይጠናቀቃል ቢባልም አምስት አመታትን ወስዷል።

ከመንገድ ፕሮጀክቶች ወጣ ስንልም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመማርያና አስተዳደር ህንጻዎች በርካታ አመታትን በመፍጀት በፕሮጀክት መዘግየት የሚጠቀሱ ናቸው። በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የሚካሄዱ ግንባታዎች በተያዘላቸው ጊዜ ገደብ ውስጥ ባለመጠናቀቃቸው በመማር ማስተማሩ ሂደት ጥላ ከማጥላታቸውም በላይ ዩኒቨርሲቲውን ለተጨማሪ ወጪ የዳረጉ ናቸው።

ሌላው በግንባታ መዘግየት ተጠቃሽ የሆነው የጳውሎስ ሆስፒታል ማስፋፍያ ግንባታ ነው። ይህ ማስፋፍያ ግንባታ ከተጀመረ 10 ዓመታትን ሊያስቆጥር ጥቂት ጊዜያት ብቻ ይቀራሉ። የግንባታው መጓተትም ሆስፒታሉ ያለበትን የህክምና መስጫ ክፍሎች እጥረት ከማባባሱም ባሻገር ሆስፒታሉን ከፍተኛ ለሆነ ወጪ መዳረጉን የተወካዮች ምክር ቤት የማህበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ማንሳቱ የሚታወስ ነው።

ግዙፉ የዓባይ ግድብም የፕሮጀክት መጓተት ሰለባ ከሆኑ ፕሮጀክቶች በግንባር ቀደምትነቱ የሚነሳ ነው። የዓባይ ግድብ የመሰረት ድንጋይ ሲቀመጥ በአምስት አመታት ውስጥ ይጠናቀቃል ተብሎ በዕቅድ ቢያዝም 13 አመታትን አስቆጥሯል።

የዓባይ ግድብ በ 82 ቢሊዮን ብር ወጪ ለመገንባት ውል ቢገባም በነበረው እጅግ ደካማ የፕሮጀክት አስተዳደር ግድቡ ከመጓተትም አልፎ የህልውና አደጋ ገጥሞት ቆይቷል። ግድቡን ከገጠመው መሰናከልና የሞት አደጋ ለማዳን በርካታ ጥረቶች ተደርገው አሁን ከ95 በመቶ በላይ ማድረስ ተችሏል። ሆኖም ቀደም ሲል በተከሰተው የግንባታ መጓተት የግድቡ ግንባታ ከ13 ዓመት በላይ ከመውሰዱም በሻገር የግንባታ ወጪውን ከሶስት እጥፍ በላይ አሳድጎታል።

የኮይሻ ግድብም ቢሆን በአምስት አመታት ውስጥ ይጠናቀቃል ተብሎ ግንባታው ቢጀመርም ዘንድሮ ስምንተኛ አመቱን ይዟል። ግድቡ በነበረበት ከፍተኛ የፋይናንስ እጥረትና ቀውስ ለወራት ቆሞ የነበረ ሲሆን ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ወደ ስልጣን ከመጡ በኋላ ችግሩ ከመሰረቱ እንዲስተካከል በመደረጉ ግንባታው በመፋጠን ላይ ይገኛል።

እንደ አጠቃላይ ከገንዘብ ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ከለውጡ በፊት በነበረው ብልሹ አሰራር ምክንያት በኢትዮጵያ የተለያዩ 102 ፕሮጀክቶች መጓተታቸው ምክንያትም 42 ቢሊዮን ብር ተጨማሪ ወጪ ጠይቀዋል።

የፕሮጀክቶች መጓተት ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ጉዳቶች ያሉት ሲሆን ፕሮጀክቶቹ ከተመደበላቸው በጀት ተጨማሪ ወጪ ይጠይቃሉ፤ በብድር የሚሰሩ ከሆነ ተጨማሪ ወለድ እንዲከፈል ያስገድዳሉ፤ ሌላ ብድር ለማግኘትም መሰናከል ይፈጥራሉ። ፕሮጀክቶቹ በወቅቱ ተጠናቀው ይሰጡት የነበረውን ጥቅምም ያሳጣሉ ።

ቀደም ሲል በነበረው አሰራር አብዛኛዎቹ ፕሮጀክቶች የሚዘገዩት በደካማ የስራ ባህል ምክንያት፤ በመንግሥታዊ ውስብስብ ቢሮክራሲያዊ አሰራር፣ቀና ትብብር አለመኖር፣ በፕሮጀክት አስተዳደር ችግርና በዕቅዶች የተፈጻሚነት ጉድለት መሆኑ በጥናት ከተረጋገጠ በኋላ በኢትዮጵያ አዲስ የፕሮጀክት አፈጻጸም መመዝገብ ጀምሯል። አንዳንዶቹ ፕሮጀክቶችም አስገራሚ በሆነ ፍጥነት ተጠናቀው ለአገልግሎት ሲበቁ መታየታቸው ሀገሪቱ በፕሮጀክቶች መጓተት ስትከፍል የነበረው ኪሳራ ከፍተኛ እንደነበር ለመገንዘብ ያስችላል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተጓተቱትም ሆነ አዲስ የተጀመሩ ፕሮጀክቶችን በማጠናቀቅ ረገድ ብዙ መሻሻሎች ታይተዋል። የግንባታ ሂደት በሪፖርት ብቻ ሳይሆን በቦታው በመገኘትም ጭምር ያሉባቸውን ተጨባጭ ችግሮች እንዲቀረፉ በማድረግ እና አዳዲስ ፕሮጀክቶችም በተያዘላቸው ጊዜና በጀት እንዲጠናቀቁ በማድረግ ረገድ አዲስ የፕሮጀክት አጨራረስ ምዕራፍ ላይ መድረስ ተችሏል።

የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አስተዳደር ከመጣ ወዲህ ለዘመናት ሲጓተቱ የነበሩ ፕሮጀክቶችን አጠናቆ ለአገልግሎት ከማብቃት ባሻገር የተጀመሩትን በፍጥነት የማስቀጠልና አዳዲስ ፕሮጀክቶችን በሚገርም ፍጥነት ለውጤት ማብቃት ተችሏል። ከዓመታት በፊት ተጀምረው በመጓተት ብሎም በመከሰም ሂደት ውስጥ የነበሩትን የዓባይ እና የኮይሻ ግድቦችን ወደ ላቀ ደረጃ ማድረስ ተችሏል። የንግድ ባንክን ህንጻ ከመቆም ታድጎ ለአገልግሎት በቅቷል። የሀገር መከላከያ ሰራዊት እና የኢንሳ መስርያ ቤቶች አምረውና ደምቀው ለአገልግሎት ክፍት ተደርገዋል።

በገበታ ለሀገር ከተገነቡት ፕሮጀክቶች መካከል አንዱ የወንጪ ደንዲ የኢኮ ቱሪዝም ማዕከል ነው። ይህ ፕሮጀክት በአጭር ጊዜ ውስጥ ከተጠናቀቁና ኢትዮጵያ ያላትን ፕሮጀክት አፈጻጸም ታሪክ ከፍ ያደረገ ትልቅ ፕሮጀክት ነው።

አዲሱ አመራር ነባር ፕሮጀክቶችን ከማጠናቀቅ አልፎ አዳዲስ ፕሮጀክቶችን ጀምሮ በመጨረሻ የብዙዎችን ይሁንታ አግኝቷል። ከእነዚህ ውስጥ ገበታ ለሀገር ተብለው ከተጀመሩና ለመዲናዋ መስህብ ከሆኑት ፕሮጀክቶች ውስጥ የአንድነት፤ የወዳጅነትና የእንጦጦ ፓርኮች ተጠናቀው የአዲስ አበባ ድምቀት ሆነዋል። የመስቀል አደባባይ ፕሮጀክትም የከተማዋ አንዱ ድምቀት ለመሆን በቅቷል።

በአይነቱ ለኢትዮጵያ የመጀመርያ የሆነውም የሳይንስ ሙዚየምም በአጭር ጊዜ ተገንብቶ የከተማው መስህብ ሆኗል። አሁን ደግሞ ሙሽራዋ አዲስ አበባ በአዳዲስ ፕሮጀክቶች ብቅ ብላለች። አዲስ አበባ የዓለም የዲፕሎማሲ መዲና፣ የአፍሪካ ዋና ከተማ፣ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ እንቅስቃሴ መናኸሪያ እንደ መሆኗ ይህን የሚመጥን ልማት እየተከወነላት ይገኛል። የልማቱ መጠርያም የአዲስ አበባ ኮሪደር ልማት ይሰኛል ።

> **ቀደም ባለው ጊዜ አንድ ባለ 12 ወለል ህንጻ ለማጠናቀቅ እስከ 15 ዓመታት ይወስድ እንደነበረ የተደረጉ ጥናቶች ያመላክታሉ። ለአብነት መሃል ፒያሳ ላይ የሚገኘው በተለምዶ አራዳ ህንጻ ተብሎ የሚታወቀው ባለ 12 ወለል ህንጻ ከ15 ዓመታት በላይ ወስዷል። በደርግ ጊዜ ተጀምሮ በኢህአዴግ ዘመነ መንግሥት የተጠናቀቀ ዓመታትን የፈጀ ህንጻ ነው**

በፍጥነትና ጥራት እየተከናወኑ ያሉ የኮሪደር ልማት ስራዎች እጅን አፍ ላይ ለመጫን የሚያስገድዱ ናቸው።

ከፒያሳ እስከ አራት ኪሎ፣ ከአራት ኪሎ እስከ ቦሌ ድልድይ፣ ከቦሌ ድልድይ በመገናኛ ወደ ሲኤምሲ፣ ከቦሌ ተርሚናል ወደ ጎሮ፣ ከሜክሲኮ ወደ ወሎ ሠፈር፣ እንዲሁም ከእንግሊዝ ኤምባሲ ወደ አራት ኪሎ የሚወስዱ ኮሪደሮች መሆናቸው ታውቋል። ስራውም በስድስት ወራት ውስጥ እንደሚጠናቀቅም ተነግሯል።

በአጠቃላይ በአምስት አቅጣጫዎች እየተከናወነ ያለው የኮሪደር ልማት ከተማዋን ከመሰረቱ የሚቀይር ነው። ከሁሉም የሚያስደስተው ደግሞ ስራውን በታያዘለት የጊዜ ገደብ ውስጥ ለማጠናቀቅ የሚደረገው ርብርብ እና ጠንካራ የስራ ባህል አግራሞትን የሚፈጥር መሆኑ ነው።

አጠቃላይ ያለውን እንቅስቃሴ ለተመለከተ የኮሪደር ልማቱ በታሰበለት ጊዜ ውስጥ እንደሚጠናቀቅ መገመት አያዳግትም። የተሽከርካሪ መሄጃ አስፋልቱን እና የእግረኛ መንገዱን ስፋት ለተመለከተውም ዓለም አቀፍ ደረጃን ባሟላ መልኩ እየተገነባ መሆኑን ያመላክታል።

የኮሪደር ልማቱን ተዘዋውሮ ለመመልከት እድል ላገኘ ሰው የሚያስገርመው ነገር የሰራተኞች የስራ ትጋትና ቅልጥፍና ነው። በዚህ ሁሉ ትጋት ውስጥ ደግሞ ስራው ጥራቱን ጠብቆ መሄዱ የሚያስገርም ነው። የተለያዩ የግንባታ ማሽነሪዎች ሲርመሰመሱ፤ሰራተኞች ደፋ ቀና ሲሉ ፤ከፍተኛ አመራሮች አቧራና ጸሃይ ፤ጨለማና ብርድ ሳይበግራቸው ክትትል ሲያደርጉ ለተመለከተ በሀገራችን አዲስ የስራ ባህል እየተፈጠረ መሆኑን መገንዘብ አያዳግተውም።

ለአብነት ከዓድዋ ሙዚየም እስከ መገናኛ ያለውን መንገድ ብንመለከት ነዋሪዎቹን አሳምኖ ከማንሳትና ቤቶቹን አፍርሶ ለግንባታ ክፍት እስከ ማድረግ የወሰደው ጊዜ ከሁለት ሳምንታት የሚበልጥ አልነበረም። በተለይም ለመንገድና ለሌሎች መሰረተ ልማቶች ግንባታ አመቺ ያልሆኑ ቦታዎችን በፍጥነት አጽድቶ ምቹ ለማድረግና ወደ ግንባታ ለመግባትም የወሰደው ጊዜ በጣት ከሚቆጠሩ ቀናት የዘለለ አይደለም። ከዚህ ቀደም በነበሩ ጊዜያት ነዋሪዎችን አሳምኖ ወደ ተዘጋጀላቸው ምትክ ቦታ ለማዘዋወርና ወደ ግንባታ ለመግባት አመታትን ይወስድ እንደነበረ በግልጽ የሚታወቅ ነው።

ዛሬ ግን እነዚህ ሁሉ ግዙፍ ስራዎች በጥቂት ቀናት ውስጥ ተጠናቀው የአስፋልት ማንጠፍ ስራ፤ የእግረኛ መንገድ ንጣፍ፤ የመንገድ ጠርዞችን የማስዋብና የማሳማር ስራዎች እጅግ በፈጠነ መልኩ ሲከናወኑ ማየት የሚያስገርም ነው።

መሸቶ በነጋ ቁጥር ተጀምረው የሚያልቁ ፕሮጀክቶችን የተመለከተ በፕሮጀክቶች መጓተት ሀገሪቱ ምን ያህል ወደኋላ እንደተጎተተች ለመረዳት አያዳግተውም። በፕሮጀክቶች መጓተት ምክንያት ቀደም ሲል ተጀምረው ከንቱ የቀሩት የያዩ ማዳበርያ፣ የስኳር ፋብሪካዎች፣ የመንገድ ፕሮጀክቶች፣ በየቦታ እንደ አሸን ተጥለው የሚገኙ የግንባታ ማስጀመርያ የመሰረት ድንጋዮች ይህችን ሀገር በብዙ ዋጋ እንድትከፍል ያደረጓት ናቸው።

እነዚህ የተጓተቱ ፕሮጀክቶች ከፍተኛ ገንዘብ የባከኑባቸው ከመሆኑም ባሻገር በከፍተኛ መጠን ባለው ወለድ በተገኘ የውጭ ብድር የተጀመሩ በመሆናቸው ሀገሪቱን እስካሁን ከፍላ ላልጨረሰችው ዕዳ ዳርጓታል። ዛሬ ግን እነዚህ ሁሉ ጉዳዮች ተረት ሆነው ፕሮጀክቶችን ጀምሮ ማጠናቀቅ ባህል እየሆነ መጥቷል።

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## ሕፃናትን በቀላሉ ማስተማር የሚያስችለው ባለድምጽ የአማርኛ ፊደል ገበታ ፈጠራ ባለሙያዎች

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ወጣት ዘርባቤል መስፍን እና ቤተሰቦቹ የማሜ መጫወቻና ፐዝሎች መስራቾች ናቸው። "የአማርኛ ባለድምጽ ፊደል ገበታ" የተሰኘ ሕፃናትን በቀላሉ ማስተማር የሚያስችል ለየት ያለ ፈጠራ መሥራት ችለዋል። ባለድምጽ የፊደል ገበታው ሥራ ላይ ካሉት ተመሳሳይ የፈጠራ ሥራዎች ይለያል፤ የፊደል ገበታው ካለምንም እገዛ በራሱ ድምጽ አውጥቶ ማስተማር ወይም ማስረዳት ይችላል።

ወጣት ዘርባቤል እንደሚለው፤ ወላጆች ልጆቻቸውን የተሻለ ትምህርት ቤት በማስገባት እንዲማሩ በተለይ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ጥሩ ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላቸው ይታወቃል። ይሁንና ሕፃናቱ እንግሊዘኛ ቋንቋን የበለጠ እያወቁ ቀስ በቀስ አማርኛ ቋንቋን እየረሱ ወይም ችላ እያሉ ይገኛሉ። ወላጆች በራሳቸው ጥረት ልጆቻቸውን ለማስተማር ቢፈልጉም፣ ከሥራ ጋር ተያይዞ ጊዜ ማግኘት እየተቸገሩ በመሆናቸው የአማርኛ ፊደላት ለማስተማር ሲቸገሩ ይስተዋላሉ።

ይህ አዲስ ፈጠራ ግን ሕፃናትን (ልጆችን) ልክ እንደ መምህር እያስተማረና ጥያቄም እያቀረበ የራሱን ሥራ መሥራት ይችላል። በፊደል ማስተማሪያው በሶፍት ዌር አማካኝነት ፊደላት ድምጽ እንዲኖራቸው ተደርጎ ተዘጋጅተዋል፤ ሁኔታው ልጆች በስልክ ወይም በስክሪን ላይ የሚያጠፉትን ጊዜ በማስቀረት ፊደላትን በመማር በቀላሉ እንዲማሩና ቁምነገሮች እንዲያውቁ ያስችላል።

የእነ ዘርባቤል የፈጠራ ሥራ የሆነው ይህ የፊደል ገበታ፣ የኢትዮጵያን ባህል እና ቴክኖሎጂ በአንድ አጣምሮ ይዟል። በቤት ውስጥ የሚሰቀል ስለሆነ ሕፃናት ፊደሉን በሚጫኑበት ጊዜ ድምጽ እያወጣ ያስተምራል። ድምጽ እያወጣ ካስተማረ በኋላ ልክ እንደ መምህር ልጆቹ ምን ያህል ተረድተዋል ወይም አውቀዋል የሚለውን ለመረዳትም ጥያቄ ያቀርብላቸዋል። ጥያቄውን በትክክል የማይመልሱ ከሆነ ወደ ቀጣይ ጥያቄ አይሸጋገርም፤ ይልቁንም ደግመው እንዲማሩ እድሉን ይሰጣል። ጥያቄውን በትክክል ከመለሱ በኋላ ጥያቄው በትክክል መመለሱን ገልጾ ወደ ቀጣይ ጥያቄዎች ይሸጋገራል።

ፊደላትን ከማስተማር ባሻገርም ቁጥሮችም ያሉት ሲሆን፤ ልጆች ቁጥሮችንም በእጃቸው ሲጫኑ ቁጥሮችን በመቁጠር በድምጽ እየጠራ እንዲማሩ ያደርጋቸዋል። ቁጥሮቹንም የተመለከቱ ጥያቄዎችንም ያቀርብላቸዋል።

ሕፃናት በመጀመሪያ ጊዜ ፊደላትን ለመማርና ለማወቅ በጣም እንደሚጓጉ ይታወቃል፤ ጠዋትም ሆነ ማታ በተመሳሳይ መንገድ በተደጋጋሚ ሲማሩ ደግሞ ቶሎ የመሰላቸት ባህሪም ይታይባቸዋል የሚለው ወጣት ዘርባቤል፤ የባለድምጽ የፊደል ገበታ ማስተማሪያው ግን ይህን ሁሉ በማስቀረት ሕፃናቱ ወደውት በፍቅር እንዲማሩ እንደሚያደርግ ይገልጻል። ይህን ፈጠራ እንዲወዱት ከሚያደርጉት መካከል አንደኛ ድምጽ አውጥቶ ማስተማሩ ነው። ሁለተኛ ጥያቄ ማቅረቡ ሲሆን፣ ሦስተኛው ደግሞ እየተዝናኑ የሀገራቸውን ባሕል እንዲያውቁ የሚረዳ መሆኑ ነው ሲል ያብራራል፡፡

ወጣት ዘርባቤል እንደሚለው፤ ባለድምጽ የፊደል ገበታ ማስተማሪያው ሙዚቃ ማዳመጥም ያስችላል። ሕፃናት ሙዚቃ ማዳመጥ ሲፈልጉ የሙዚቃውን ቦርድ በእጃቸው በመጫን ከፈተው ማዳመጥ ይችላሉ። መዚቃውም በውስጡ የኢትዮጵያን ባሕላዊ እሴቶች፣ ወግ እና ትውፊቶች የሚያንጸባሩቁ መዝሙሮች፣ ተረቶች፣ ምሳሌዊ አነጋገሮች፣ ግጥሞች ፣ አባባሎች ፣ የአባቶች ምክር እና ሌሎች ከ20 በላይ ትራኮች የተካተቱበት ነው። ለአብነት የሙዚቃ መጫወቻውን ሲጫኑ በመጀመሪያ ላይ የሚያዳምጡት የኢትዮጵያን ሕዝብ መዝሙር ነው። ሕፃናቱም መዝሙሩን ያለሰው እገዛ ተምረው በቃላቸው ይዘው ወደ ትምህርት ቤት እንዲገቡ ያስችላል፡፡

«በዚህ የባለድምጽ ፊደል ገበታ ማስተማሪያ አማካኝነት ሕፃናት ሦስቱን ማለትም አማርኛ የማዳመጥ፣ የማንበብ እና የመናገር ክህሎቶቻቸውን ማሳደግ ይችላሉ» የሚለው ዘርባቤል፤ የተቀረውን አራተኛውን የመጻፍ ክህሎት ደግሞ በቤታቸው ሆነው እዚያው በፊደል ገበታው ላይ ባለው በነጭ ሰሌዳ (ኃይት ቦርድ) ላይ ጽፈው በመለማመድ እያንዳንዱን




**የአማርኛ ባለድምጽ የፊደል ገበታ**

ፊደል ለማወቅ ያስችላቸዋል ሲል ያብራራል። የፊደል ገበታው የተሰራበት ቁስ ፕላስቲክ መሆኑን ጠቅሶ፣ በቀላሉ በእጃቸው ወይም በሶፍት ካልሆነም በዳስተር መጥፋት እንደሚችሉ አስረድቷል።

እነ ዘርባቤል፤ ይህን የፈጠራ ሥራ ለመሥራት መነሻ የሆኗቸው በአሁኑ ወቅት በአቅራቢያቸው የሚመለከቷቸው በስልክ ስክሪን ላይ የተጠመዱ ሕፃናት መሆናቸውን ተናግሯል። ሕፃናት ስልክ ላይ ካላቸው ጥገኝነት ተላቅቀው ፊደላትን በቀላሉ መማር የሚችሉበትን መንገድ ለመፍጠር እንዲሁም ወላጆች ልጆቻቸውን ፊደል ለማስቆጠር ያለባቸውን ጫና ለመቀነስ በማሰብ ይህን መፍትሔ ማግኘታቸውን ይገልጻል። "ከምንም በላይ ግን ችላ ያልናቸውን የሀገራችንን የአማርኛ ፊደላት በቀላሉ መንገድ እንዲያወቁት ተብሎ የተዘጋጀ የፈጠራ ሃሳብ ነው » ይላል።

የባለድምጽ ፊደል ገበታ ማስተማሪያው ሶፍትዌር፣ ሚሞሪእና ቺትስን አካቶ የያዘ ነው። ከእያንዳንዱ ፊደል ጋር የተያዙ ቦርዶች ስላሉ ቦርዱ ከሚሞሪው ጋር ተገናኝቶ ድምጽ ይፈጥራል። ለዚሁ ተብሎ ከተዘጋጀው ፕሮግራም ጋር እንዲገናኝ ተደርጎ ድምጹ ወጥቶ እንዲሰማ ይደረጋል።

« የፈጠራ ሃሳብ እንደመጣልን ጥናት አድርገናል፤ የጥናቱ ውጤት የአማርኛ ፊደላት በሕፃናት ዘንድ እየተረሱ መምጣታቸውን አመላክቶናል» የሚለው ዘርባቤል፤ ይህ ችግር ደግሞ ለትምህርት ቤቶች እና ለወላጆች ብቻ የሚተው እንዳልሆነ ገልጾ ሕፃናቱ በቀላሉ ከስልክ የሚላቀቁበትን እና የወላጆች ጫናም የሚቀነስበትን መንገድ መፍጠር እንደሚያስፈልግ አመንን ሲል ያብራራል። ለዚህም ሕፃናት እየተጫወቱ በቀላሉ ፊደል የሚማሩበትን ባለድምጽ የፊደል ገበታ እውን ማድረጋቸውን አስታውቋል።

የፊደል ገበታው አሁን መሠረታዊ የአማርኛ ፊደላትን ድምጽ ብቻ እያወጣ እንዲጠራ ሆኖ የተሰራበት ሁኔታ የሥራው ክፍል አንድ መሆኑን አብራርቶ፣ በቀጣይ በክፍል ሁለት ደግሞ ይህን በማስፋት ሞክሼ ፊደላትን፣ የፊደላትን ቀመርና ሌሎችንም እንዲያካትት በማድረግ እንደሚሰራ ዘርባቤል አመላክቷል። ሌሎች በጣም ብዙ ሥራዎችን ለመሥራት ማቀዳቸውንም ይናገራል።

ይህን ማስተማሪያ ከአንድ ዓመት እስከ 6 ዓመት ያሉ ልጆች ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ አመልክቶ፤ አንድ ሕፃናን ማስተማሪያውን ለመጠቀም ሲፈልግ እንዴት መጠቀም እንደሚችል የሚያሳዩ ቪዲዮዎች መዘጋጀታቸውንም አስታውቋል። ባለድምጽ ፊደላት ማስተማሪያው በፓኬጅ የተዘጋጀ መሆኑን ተናግሮ፤ ፓኬጁ ሲከፍት እንዴት መጠቀም እንደሚቻል የሚያሳይ መመሪያ ውስጡ እንዳለውና በመመሪያ መሠረት በቀላሉ ለመጠቀም እንደሚቻል አስገንዝቧል፡፡

እነዘርባቤል ማስተማሪያውን መሸጥ ከጀመሩ አንድ ዓመት ሞልቶቸዋል። እስካሁን 600 ቅጂዎችን ሸጠዋል። ማስተማሪያውን መጠቀም በጀመሩ ወላጆች በኩል ምንም ዓይነት ቅሬታ ገጥሞቸው እንደሚያውቅ ይናገራል። እንዲያውም ወላጆች በጣም እንደተደሰቱበት ሕፃናትም ወደውት እየተማሩበት እንዲሆን በሰበሰቡት አስተያየት ማወቃቸውን ይገልጻሉ፡፡

ይህ ማስተማሪያ በአዲስ አበባ ከተማና በሀገሪቱ የተለያዩ ከተሞች እየተሰራጨ መሆኑንም ዘርባበል ያመላክታል። ማስተማሪያውን ለሚፈልጉ ሰዎች ባሉበት ቦታ ሆነ እንዲያገኙት እየተደረገ መሆኑን ጠቅሶ፤ በአቅራቢያቸው ለሚገኙት ደግሞ ባሉበት በማድረስ፣ ርቀው ላሉት ደግሞ በፖስታ ቤት በኩል እንዲደርሳቸው እያደረጉ እንደሆነ አስታወቋል፡፡

ወጣቱ የፈጠራ ባለሙያ እንዳብራራው፤ ይህ ማስተማሪያ የሚመረተው በቻይና ነው፤ በዚያ ሲመረት የማምረቻ ዋጋው ቅናሽ ያለው ቢሆንም፣ ሀገር ውስጥ እስኪገባ ድረስ ያለው ወጪ ዋጋውን ከፍተኛ አድርጎታል። ለዚህም አንዱ ምክንያት ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ ሶስት እጥፍ ቀረጥ የሚከፈልበት መሆኑ ነው። ስለዚህ የአንዱ የፊደል ገበታ ዋጋ 2ሺ ብር ነው።

አሁን ለጀማሪ የፈጠራ ባለሙያዎች(ስታርትአፖች) ትኩረት እየተሰጠ መሆኑን ጠቅሶ፣ በሕጉ ላይ ማሻሻያ የሚደረግ ከሆነ አሁን ካለው ዋጋ በጣም ይቀንሳል፤ ያንን ተከትሎም ለሁሉም ተደራሽ ማድረግ ይቻላል ሲል አብራርቷል፡፡

የባለድምጽ የአማርኛ የፊደል ገበታን ለመሥራት የሚያስፈልጉት ነገሮች ዲዛይን፣ ሶፍትዌር፣ በውስጡ የሚገቡት ድምጾቹ ሲሆኑ፤ እነዚህ ሁሉም እዚሁ ተሰርተው ለፕላስቲኩ ሲባል ብቻ ወደ ቻይና እንደሚላክ የሚገልጸው ዘርባቤል፤ ቻይና በሚመረትበት ጥራት በሀገር ውስጥ ፕላስቲኩን የሚያመርት አምራች ቢኖር ሁሉንም በቀላሉ ሀገር ውስጥ መጨረስ ይቻል እንደነበር አስረድቷል፡፡

አሁን ላይ ሀገር ውስጥ ፕላስቲክ የሚያመርቱ እንዳሉ ጠቅሶ፣ እነሱ ግን ለዚህ ማስተማሪያ መሥሪያ የሚውል ጥራቱን የጠበቀ ፕላስቲክ ግን ለማግኘት እንዳልቻሉ አመላክቷል። የሀገር ውስጦቹ ፕላስቲኮች በፍጥነት የሚቀደዱና የሚበላሹ መሆናቸውን ገልጾ፣ ማስተማሪያውን የሚጠቀሙት ሕፃናት እንደመሆናቸው መጠን ፕላስቲኩ ረጅም ጊዜ ሊያገለግል የሚችል አለበት፤ ወላጆችም የሚፈልጉት እንዲህ ዓይነቱን ነው፤ የቆይታው ጊዜ ያስጨንቃቸዋል ሲል ያብራራል፡፡

"እኛም እንደወላጆች የሚያስጨንቀን ጥራቱን የጠበቀ መሆኑና የቆይታ ጊዜው ነው። የሚፈለገውን ጥራት ባሟላ መልኩ ሀገር ውስጥ የሚያመርት አምራች ካለ አብረን ለመሥራት ፈቃደኞች ነን " ሲሉም አስታውቋል፡፡

እሱ እንዳብራራው፤ ከቻይና የሚመጣው ማስተማሪያ በጣም ረጅም ጊዜ ይቆያል። ባትሪው ቢያንስ ከስድስት ወር እስከ አንድ ዓመት ያህል ሊያገለግል ይችላል። ፈጽሞ አይጨማደድም፤ ውሃ ቢገባበት እንኳን መከላከያ የተገጠመለት በመሆኑ አይበላሽም። በቤት ውስጥ የሚሰቀል በመሆኑ በጣም ረጅም ጊዜ ይቆያል፡፡

"ማስተማሪያው ሕፃናት ራሳቸው በቀላሉ ሊማሩበት ይችላሉ። ከወላጆች የሚጠበቀው ማስተማሪያው የሚጠቀምበትን ሦስት የሪሞት ባትሪ ማስገባት ብቻ ነው። ከዚያ ሕፃናት በባህሪያቸው መነካካትና መሞከር ስለሚወዱ ሲነካኩትና ሲሞክሩ በራሳቸው ሊያውቁት የሚችሉ ነው" ይላል፡፡

"ባለፈው ዓመት ሥራው ከጀመርን አንስቶ ለስድስት ወራት ያህል አብዛኛውን ሥራ የሠራነው ሳይንስ ሙዚየም ውስጥ ነው፤ ከሙዚየሙ ትልቅ ድጋፍ አግኝተናል። የማስተዋወቅ ሥራ ሰርተናል፤ አብዛኛዎቹን ምርቶችም እዚያው መሸጥ ተችሏል» የሚለው ዘርባቤል፤ አሁንም ከወር በፊት በጀመሯቸው ማህበራዊ ሚዲያዎች እና ቲክቶክ ላይ እያስተዋወቁ እንደሚገኙ ጠቁሟል፡፡

በዚህ የፈጠራ ሥራ በአዲስ አበባ በተካሄደ የስታርትአፖች ውድድር ላይ አሸናፊ መሆናቸውን ጠቅሶ፤ የፈጠራ ባለቤትነት መብትን ከኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት ማግኘት ተመዝግበው እየጠበቁ መሆኑን ተናግሯል።

እነዘርባቤል ትኩረታቸውን ሕፃናት ላይ ስላደረጉ ከዚህ ፈጠራ በተጨማሪ ሕፃናት ፐዝሎችን በመገጣጠም የሀገራቸውን ታሪክ በቀላሉ እያወቁ እንዲያድጉ የሚያደርጉ ፐዝሎችን ለየት ባለመልኩ አዘጋጅተዋል። ፐዝሎቹን ዲዛይን፣ ምስልና ግጥም በማዘጋጀት አሳትመው ሕፃናት በቀላሉ የሀገራቸውን ታሪክ እንዲያውቁ እያደረጉ ነው።

ለአብነትም አትሌት አበበ ቢቂላን በተመለከተ ፐዝል አዘጋጅተዋል። ሕፃናት የአበበ ቢቂላን ማንነት ለማወቅ ሲፈልጉ ምስሉን የሚያሳይና ምንድነው የሰራው የሚለውን እንዲያወቁ የሚያስችል ነው። ፓዝሉም በአማርኛና በእንግሊዘኛ ግጥም የተዘጋጀ ነው። ፐዝሉን መገጣጠም የሕፃናት አእምሮ የበለጠ እንዲሰፋ ይጠቅማል፤ ገጥመው ከጨረሱም በኋላ ይሄ ምንድነው ብለው የሀገራቸውን ታሪክ እንዲያወቁ ለማድረግ ይረዳል ሲል ዘርባቤል ያብራራል። የሀገራችንን ታሪካዊ ቦታዎች የተመለከቱ ፐዝሎች በሀገሪቱ እንዳሉ ጠቅሶ፣ እነርሱ ይህን አሻሽለው በተለየ መልኩ ማዘጋጀታቸውን ያመላክታል።

እሱ እንዳብራራው፤ ይህ የፊደል ገበታው የመጀመሪያ ሥራ ነው፤ እነ ዘሩባቤል ወደፊትም ከዚህ በተሻለ መልኩ የአማርኛን ፊደሎች ማስተማር የሚቻልበትን ዘዴ ለመፍጠር ይሰራሉ። በተለይ ሕፃናትን ከስልክ በማራቅ ባሕሉን መሠረት ባደረገ መልኩ ቴክኖሎጂን ጨምሮ የሀገራቸውን ባህልና ሥርዓት በእጃቸው ሳይቀር ዳስሰው እንዲውቁ፣ እንዲማሩበትና እንዲለምዱ ለማድረግ ብዙ ሥራዎችን ይሰራሉ። በተጨማሪ ሌሎች ለሕፃናት የሚሆኑ ሥራዎችን ለመሥራት እየተዘጋጁ ናቸው፡፡

ወጣት ዘርባቤል ፤ በተለይ አሁን ላይ ሥራ ለሚጀምሩ ጀማሪ የሥራ ፈጣሪዎች (ስታርትአፖች) ከዚህ በላይ ጥሩ እድል የሚያገኙ አይመስለኝም ፤ የፈጠራ ሃሳብ ያላቸው ሥራ ፈጣሪዎች ሀሳቡ እያላቸው የተቀመጠውን መስፈርት ለማሟላት ባለመቻላቸው ሲቸገሩ ቆይተዋል። በመሆኑም አሁን ላይ አብዛኛዎቹ ችግሮች በሚባል ደረጃ እንዲቀረፉ የሚያደርጉ የሕግ ማሻሻያዎች እየወጡ ናቸው፤ ሃሳብ ያላቸው የፈጠራ ባለሙያዎች ያላቸው ሃሳብ ይዘው ሥራቸውን መጀመር ይችላሉ ሲል ምክረ ሃሳቡን ሰጥቷል፡፡

## ወቅታዊ ትንታኔ

# የመኖሪያ ቤት ኪራይ አዋጁ ፋይዳና ተግዳሮት

**ምሕረት ሞገስ**

መጋቢት 24 ቀን 2016 ዓ.ም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባካሄደው ስብሰባ የመኖሪያ ቤት ኪራይ ቁጥጥርና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1320/2016ን አፅድቋል። አዋጁ በፀደቀበት ወቅት አላማው በመኖሪያ ቤት ኪራይ ዋጋ መናር የሚከሰተውን የኑሮ ውድነት ጫና በመቀነስ የመኖሪያ ቤት ኪራይ ዋጋን ከተከራዮች አቅም ጋር የተመጣጠነ ለማድረግ ያለመ መሆኑ ተገልጿል።

በተጨማሪ የመኖሪያ ቤት ኪራይን ከአከራዩ ብቸኛ ፍላጎት ማውጣትና በመኖሪያ ቤት እጥረት እየተፈጠረ ያለውን ውጥረት ለማርገብ ስለመሆኑም ተብራርቷል። አዋጁ የቀድሞው የመኖሪያ ቤት የአከራይ እና የተከራይ የውል ግንኙነት ላይ ለውጦችን ይዟል።

ቀደም ብሎ የመኖሪያ ቤት ኪራይ ውል በቃል ይደረግ ነበር። በጽሑፍ ቢደረግም በአከራዩና በተከራዩ እጅ የውሉ ቅጅ ይቀመጣል እንጂ፤ ውሉን የሚመዘግብ ራሱን የቻለ አካል አልነበረም። በአዲሱ አዋጅ አንቀፅ 4 መሠረት ግን የመኖሪያ ቤት ኪራይ ውልን በጽሑፍ ማድረግ ግዴታ ነው። በተጨማሪ ውሉም በተቆጣጣሪው አካል ተረጋግጦ መመዘገብ በአስገዳጅነት ተቀምጧል።

በጽሑፍ የተደረገ ነባር የመኖሪያ ቤት ኪራይ ውል አዋጁ በወጣ በ30 ቀናት ውስጥ አከራይ እና ተከራይ ወይም ወኪሎቻቸው ተቆጣጣሪው አካል ዘንድ ቀርበው ውሉን አቅርበው የማረጋገጥና የማስመዝገብ ግዴታ አለባቸው። በተጨማሪ ያልተረጋገጠና ያልተመዘገበ የመኖሪያ ቤት ኪራይ ውል እንዳልተደረገ ይቆጠራል ወይም በሌላ አገላለፅ አከራይም ሆነ ተከራይ ባልተመዘገበ የኪራይ ውል መብታቸውን ሊጠይቁ አይችሉም የሚል ድንጋጌ ሰፍሯል።

ይህ ብቻ አይደለም አዋጁ የኪራይ ውሉን የማረጋገጥና የማስመዝገብ ግዴታቸውን ያልተወጡ አከራዮችና ተከራዮች ላይ የገንዘብ ቅጣት እንደሚጣል ደንግጓል። የገንዘብ ቅጣት መጠኑ የተቆጣጣሪው አካል በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ሲሆን፤ ምንም ቢሆን ግን ከሦስት ወር የቤቱ ኪራይ እንደማይበልጥ አዋጁ ገደብ አስቀምጧል።

የመኖሪያ ቤት ኪራይ ተቆጣጣሪ ድሬዳዋና አዲስ አበባ ከተማን ጨምሮ በሁሉም ክልሎች የሚሰየም አካል ነው። አዋጁ ተፈፃሚ የሚሆነውም አዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማን ጨምሮ ተጠሪነታቸው ለክልል በሆኑ ከተሞች ወይም ማዘጋጃ ቤት በተቋቋመባቸውና በሕግ ስልጣኑ በተሰጠው አካል ከተማ ተብለው በተሰየሙ ስፍራዎች በሚፈፀሙ የመኖሪያ ቤት ኪራዮች ላይ ነው ተብሏል።

ይህ አዋጅ ከወጣ በርግጥ አንድ ወር አለፈው። ምን ያህል ተፈፃሚ እየሆነ ነው የሚለው አጠያያቂ ቢሆንም፤ የአዋጁን አስፈላጊነት ጥቅም እና ጉዳቱን እንዲሁም አዋጅ ወጥቶ አለመፈፀሙ የሚያስከተለውን ጉዳት በተመለከተ የምጣኔ ሀብት ምሁራን የሚሉት አላቸው።

የምጣኔ ሀብት ምሁሩ ፕሮፌሰር ጣሰው ወልደሃና መንግሥት የመኖሪያ ቤት ኪራይን መቆጣጠሩ መልካም እና በሌሎች ሀገሮችም የተለመደ መሆኑን ጠቁመው፤ የኪራይ ዋጋ ለመወሰን መሞከር እና ሰው ባፈራው ንብረት ላይ ማዘዝ ግን ከነፃ ገበያ ሥርዓት አንፃር ትክክል አለመሆኑን ይገልፃሉ። የመኖሪያ ቤት ኪራይ ዋጋ እንዲቀንስ ዋነኛው መፍትሔ በርካታ ቤቶች እንዲገነቡ ማድረግ ነው ይላሉ።

ለቤት አከራዮች የታክስ ማበረታቻ መስጠት እንጂ፤ ታክስ እየሰበሰቡ፣ መሬት እና የግንባታ ቁሳቁስ እጅግ ውድ ሆኖ የመኖሪያ ቤት ኪራይ ዋጋን መተመን ብዙ የሚያስኬድ አለመሆኑን ያስረዳሉ። መጨረሻ ላይ አከራዩ የራሱን መንገድ ሊፈጥር እንደሚችል ይናገራሉ። ለምሳሌ አለማከራየት እና ቤት ለመገንባት እና ለማከራየት የሚያስበውም ቤት እንዳይገነባ ስለሚያደርገው በተዘዋዋሪ ተከራይ የሚጎዳ ይሆናል ይላሉ።

እንደ ፕሮፌሰር ጣሰው ገለፃ፤ ቁጥጥር አይደረግ ማለት አይደለም። ሥርዓት መኖር እንዳለበት አይካድም። ነገር ግን መንግሥት በየዓመቱ ተመን ማውጣቱ የሰዎችን መብት ይጋፋል። ሰዎች የሚጨምሩት የራሳቸውንም ወጪ አስታከው ነው። ቤት ሠርቶ በማከራየት የሚተዳደር ሰው እንዳለ መታወቅ አለበት። የተከራይ መብት ብቻ ሳይሆን፤ የባለሀብቱ የአከራዩም መብት ሊታሰብ ይገባል። በእዚህ በኩል ገበያውን ነፃ መልቀቅ እንጂ ገበያውን የሚያውከውን ነገር መንግሥት ከመቆጣጠር ውጪ ወደ



**የመኖሪያ ቤት ኪራይ አዋጁ የቤት ኢንቨስትመንቱን ፈጠራ እንዲኖረው ከማድረግ በተጨማሪ ቴክኖሎጂ እንዲያካትት በማድረግ ምክንያታዊ ጭማሪ እና ትርፍ እንዲኖር ያደርጋል**

ሌላ መግባቱ ትክክል አይደለም።

ነገር ግን በዋናነት በተለይ ተከራይን በየሶስት ወሩ እና በየስድስት ወሩ ማስወጣቱ ትክክል አይደለም። በማለት፤ በዚህ ላይ መንግሥት አዋጁን ማውጣቱ ተገቢ ነው የሚል እምነት እንዳላቸው ይገልፃሉ። ይህ ቢሆንም የተወሰኑ ግለሰቦች ገበያውን እንዳይቆጣጠሩት ከማድረግ ውጭ፤ በአቅርቦት እና ፍላጎት መካከል ያለውን በማመጣጠን ነፃ ገበያው እንዲወስነው ብቻ መፍቀድ ተገቢ ነው ይላሉ፡፡

ግብርን በተመለከተ ግን ያለ ምንም ጥያቄ ቤት እያከራዩ ግብር የማይከፍሉትን በደንብ መቆጣጠር እና ተከታትሎ ማስከፈል የመንግሥት ኃላፊነት መሆኑን አስረድተዋል። መንግሥት በምንም መልኩ ማንገራገር የሌለበት መሆኑን በመግለፅ፤ ማንኛውም ሰው ማወቅ ያለበት የትኛውም የመንግሥት አገልግሎትን ለማግኘት ግብር መክፈል ግድ መሆኑን ነው ብለዋል። በዚህ በኩል አዋጁ ተገቢ ነው የሚል እምነት እንዳላቸው አመልክተዋል፡፡

‹‹በርግጥ አዋጁ ከወጣ አንድ ወር አልፎታል። እየተፈፀመ መሆኑ ግን አጠራጣሪ ነው። ብዙዎች አዋጁ ላይ ያለውን ዝርዝር ጉዳይ የሚውቁት አይመስለኝም። ነገር ግን ደግሞ አለማወቅ ከተጠያቂነት አያድንም፡፡›› በማለት የተናገሩት ፕሮፌሰር ጣሰው፤ ነገር ግን የመገናኛ ብዙሃኑ በአዋጁ የተቀመጡትን አስገዳጅ ጉዳዮች ማስተዋወቅ አለባቸው። በመንግሥት በኩል ለማስፈፀም የሚረዱ መመሪያዎች ምንም እንኳ ጊዜ ቢፈጁም ፈጠን ብለው መዘጋጀት እንዳለባቸው ጠቁመዋል።

ሌላኛው የምጣኔ ሀብት ምሁር ተሾመ አዱኛ ዶ/ር በበኩላቸው እንደሚያስረዱት፤ በቅድሚያ ስለአዋጁ ከመነጋገር በፊት ቤት ምን እንደሆነ መረዳት ይገባል። ቤት ለገበያ የሚቀርብ ነው። በተጨማሪ ሰው ቤት ውስጥ የመኖር መብት አለው። ስለዚህ በሁለት በኩል መታየት አለበት ይላሉ። ገቢ ማግኛ እና የሰዎች መብት ጉዳይ መሆኑን መረዳት ይገባል ካሉ በኋላ፤ ነገር ግን አንዳንዶች ለገበያ ብቻ የሚቀርብ ያደርጉታል፤ ስለዚህ በፈለግኩት ዋጋ እንደፈለግኩት ማከራየት እችላለሁ ይላሉ። ሌሎች ደግሞ መብት ብቻ አድርገው ያስቡታል ሁለቱም ትክክል አይደሉም ይላሉ።

እንደ ዶ/ር ተሾመ ገለፃ፤ አዋጁ ከላይ የተጠቀሱትን ማለትም ለገበያ ማቅረብንም ሆነ የሰው ልጅ የመኖሪያ ቤት የማግኘት መብቱን ሁለቱንም አጣጥሞ የያዘ ነው። የቤት ኪራይ ገበያው እንዲረጋጋ እና በአከራይ እና በተከራይ መካከል መልካም ግንኙነት እንዲኖር የሚያደርግ ነው። በገበያው መካከል የሚመለከታቸው አካሎች አሉ። ተከራይ እና አከራይ ባህሪያቸው የሚወሰነው ባለው የሕግ ጥራት እና ውጤታማነት ነው። በኢትዮጵያ ደረጃ ይህ ሕግ ባለመኖሩ ግንኙነቱ አንዱ ሌላውን እንዲጨቁን የሚያደርግ ነበር። ምክንያቱም ተከራዩንም ሆነ አከራዩን መሃል ላይ የሚይዛቸው ምንም ዓይነት ሕግ የለም። አሁን ግን ይህ ሕግ ወጥቷል።

በሌላ በኩል ሕግ ይውጣ ሲባልም፤ ነፃ ገበያ በመሆኑ አይቻልም የሚሉ አሉ። ነገር ግን ነፃ ገበያ በመሆኑ እንደፈለግን እንሆናለን የሚባል ነገር የለም። በየትኛውም ዓለም ነፃ ገበያ የሚባል ነገር የለም። በማለት የፕሮፌሰር ጣሰውን ሀሳብ ይቃወማሉ። የመኖሪያ ቤት ሲባል የጋራ መኖሪያ ቤቶችን እና የሪል እስቴት የኪራይ ገበያን የሚካትት ሲሆን፤ እነዚህ አካባቢ ያለው ዋጋ በየጊዜው እጅግ ተቀያያሪ እና በጣም የተጋነነ ነው ይላሉ።

ኪራይ ማለት አንድ ሰው ላወጣው ወጪ የሚፈፀም ክፍያ ነው። ነገር ግን አገልግሎቱ ላይ ምንም ዓይነት ጭማሪ ሳይደረግ ማለትም ቤቱ ሳይታደስ ወይም ተጨማሪ ግብዓት ሳይሟላለት ክፍያው ግን እጅግ እንደሚጨምር ተናግረዋል። እንደዚህ ዓይነት ነፃ ገበያ እንደሌለ በመጠቆም፤ ከእዚህ አንፃር አዋጁ መውጣቱ እጅግ መልካም መሆኑን እና በአግባቡ ከተተገበረ ሥርዓት እንደሚያስይዘው ገልጸዋል።

የቤት ኪራይ ዋጋውን ከአከራዩም ሆነ ከተከራዩ በላይ የሚወስኑት ኮሚሽናቸውን ብቻ አስበው የሚንቀሳቀሱት ደላሎች እንደነበሩ በማስታወስ፤ አዋጁ በቤት ልማት ውስጥ ምንም ዓይነት ሚና የሌላቸው ደላሎች ገበያው ላይ እንዳይጫወቱ ትልቅ መፍትሔ ነው ብለዋል። በአግባቡ ከተተገበረ ለመንግሥት ብቻ ሳይሆን አከራዩም ሆነ ተከራዩ ተጠቃሚ እና ስኬታማ ይሆናሉ የሚል እምነት እንዳላቸውም አመልክተዋል።

እርሳቸው አውሮፓ ሀገራት ሲሔዱ እንደተመለከቱት፤ የቤት ኪራይ ዋጋ ማንም ሰው እንደፈለገው እንደማይጨምር ገልፀው፤ ነገር ግን አከራይ ኢንቨስት በማድረጉ እንዲበረታታ በተወሰነ መልኩ ታሳቢ ይደረጋል ብለዋል። ከግብር አንፃርም ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙዎቹ አከራዮች መደበኛ ባለመሆናቸው እንደማይከፍሉ ጠቁመው፤ የአዋጁ መውጣት የመኖሪያ ቤት ገበያን ሥርዓት ከማስያዝ ባሻገር ግብር በአግባቡ እንዲከፈል ያግዛልም ብለዋል፡፡

ይህ አዋጅ የመኖሪያ ቤት ኪራይ ዋጋን ለማረጋጋት ያስችላል የሚል ተስፋ ቢኖርም፤ በአንድ ወር ውስጥ አዋጁ ላይ ተካተው ይፈፀማሉ የተባሉት ጉዳዮች በሙሉ አዋጁን ያወጣው አካል ቶሎ ማስተግበር አለበት። የአንድ መንግሥት ጥራት እና ጥንካሬ የሚለካው የሚያወጣው ሕግ በጊዜ እና በሰዓቱ ሲተገበሩ መሆኑን በማስታወስ፤ አለመተግበሩ የሥነ ልቦና ጉዳትም እንደሚያስከትል አመልክተዋል።

ሕገወጥነትን ሥርዓት ለማስያዝ የወጣው ሕግ የማይተገበር ከሆነ መንግስት ይናገራል እንጂ አይሠራም የሚል ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ በመሆኑ ውስንነቶች ቢኖሩበትም በሂደት እየታረመ እንደሚሄድ በማሰብ ወደ ተግባር መሸጋገር አለበት ብለዋል። ያለበለዚያ ሕገወጦቹን የበለጠ ሊያጠናክር እንደሚችል ጠቁመዋል፡፤

ከኢኮኖሚ አንፃርም የመኖሪያ ቤት ኪራይ፤ ሥርዓት ያለው ቁጥጥር እንደሚያስፈልግ በማመላከት ያለበለዚያ የሀብት ፈጠራው እና የተፈጠረውን ሀብት አጠቃቀም ተመልሶ ኢኮኖሚውን ሊጎዳ ስለሚችል እንደዚህ ዓይነት አዋጆች ሲወጡ፤ በመጀመሪያ ደረጃ የቤት ተከራዮች ቤት ኪራይ ከመክፈል ባሻገር ሕይወት እንዲኖራቸው ያስችላል ብለዋል።

ለመኖሪያ ቤት ኪራይ አንዳንድ ሰው የሚከፍለው ሙሉ ደሞዙን አንዳንዱ ደግሞ ከግማሽ ደሞዙ በላይ በመሆኑ ተከራዮች ሌላ ኑሮ እንደማይኖራቸው በማስታወስ፤ ገንዘብ መቆጠብ እና ንብረት መያዝ አይችሉም። መማር እንኳን የማይችሉ አሉ። ስለዚህ የሕብረተሰብ የኑሮ ጥራት ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። ይሄ ማህበረሰብ ይህንን አገኘ ማለት የሀገሪቷ ዜጎች የኑሮ ደረጃ እና ድህነት ቅነሳ የሕዝቦች ደስታ ወይም የርካታ ደረጃ ይጨምራል ብለዋል።

አከራዮች ተመጣጣኝ ትርፍ ካገኙ በዘርፉ ኢንቨስት ለማድረግ ይበረታታሉ። ለምሳሌ ዱባይ ውስጥ ቤት ለመከራየት ስንት ክፍል ነው ብቻ ሳይሆን፤ ቤቱ ምን አሟልቷል? ጥራቱስ? እየተባለ ጥያቄ ይቀርባል። ዋጋውም በቤቱ ጥራት እና ግብዓት እንዲሁም ውበት ልክ ይሆናል። በኢትዮጵያ ውስጥ ግን ያለው ጭማሪ አርቴፊሻል በመሆኑ ውድድር አይኖርም። ፈጠራ አይኖርም፤ ኢንቨስት እያደረጉ ሳይሆን ዝም ብለው ምንም እሴት ሳይጨምሩ እያጋነኑ ዋጋ የሚቆልሉ በመሆኑ አዋጁ ይህንን ይቀይረዋል።

የመኖሪያ ቤት ኪራይ አዋጁ የቤት ኢንቨስትመንቱን ፈጠራ እንዲኖረው ከማድረግ በተጨማሪ ቴክኖሎጂ እንዲያካትት በማድረግ ምክንያታዊ ጭማሪ እና ትርፍ እንዲኖር ያደርጋል። ሌላው መንግሥትም ምን ያህል አከራይ እና ተከራይ እንዳለ እንዲያውቀው ያስችላል። መንግሥት ከቤት ኪራይ ግብር የሚያገኘው ገቢ እጅግ ትንሽ በመሆኑ፤ ለመንግሥትም ከመኖሪያ ቤት ኪራይ የሚያገኘውን ገቢ ይጨምርለታል። ይህ ማለት ከገቢ ግብር ብቻ የነበረውን ገቢ የሚያሻሽለው ይሆናል። ስለዚህ አዋጁ ከተከራይ ብቻ ሳይሆን ከአከራይም እንዲሆን ከመንግሥትም አንፃር ጥቅሙ ከፍተኛ መሆኑ ላይ ምንም ዓይነት ክርክር እንደሌለው ባለሙያዎቹ አስረድተዋል።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# የድምፅ አልባዋ ልጅ አያት

አስመረት ብስራት

ሰሜን ሸዋ ሰላ ድንጋይ የተባለች ቦታ ነው የተወለዱት። የስልሳ ሰባት ዓመት አዛውንት የሆኑትን ወይዘሮ ወርቅነሽ አሰፋን ያገኘናቸው በትኩረት ለሴቶችና ለሕፃናት ማህበር የልዩ ፍላጎት ያላቸው ሕፃናት ማዕከል ውስጥ ለፋሲካ በዓል የተዘጋጀ የስጦታ መርሃ ግብር ላይ ነበር።

አጠገባቸው ተቀምጬ ማውራት ስንጀምር ነበር ሳግ በተቀላቀለው ድምፅ ጨዋታቸውን የጀመሩት። መከፋት ሞልቶ ሊፈስ ያለበት ሰዓት ላይ ደርሼ ማባበል እስኪከብደኝ ድረስ ብሶታቸውን አንድ በአንድ ዘረዘሩልኝ። መከፋት ቀንድ አውጥቶ ነፍስ ዘርቶ ፊቴ ሲቆም ተመልከተኩት። ተነግሮ የማያልቅ ህዘን ውስጣቸው ሞልቶ አንደበታቸው ከሚናገረው በላይ መሆኑን መላ አካላቸውን የሚንጠው በእንባ የታጀበ ድምፅ ከቃል በላይ መከራ መሸከማቸውን ያሳያል።

አንድ ቀን ልጅን ሲያተኩሰው መያዣ መጨበጫ ለሚጠፋት እናት ይህ ስሜት ምን ማለት እንደሆነ አይጠፋትም። ለአስራ ሶስት ዓመታት ከዛሬ ነገ ለውጥ ይመጣል በማይባልበት ሁኔታ ልጅ ሳትናገር፤ ሳትራመድ፤ እንደ ልቧ ሳትመገብ፤ እንደ ልጅ ቦርቃ ሳታድግ ከመመልከት የላቀ ውስጥን የሚሰብር ህዘን ከወዴት ይገኛል።

በተለይ አያቶች ለልጅ ልጆቻቸው ካላቸው ፍቅር አንፃር ሲታይ ህመሙ ገዝፎ ይታያል። ለዚህም ማሳያ ወይዘሮ ወርቅነሽ ናቸው። ወይዘሮዋ ከበዛው መከፋት ከእንባው መለስ ያወጉኝን ታሪካቸውን እነሆ ብያለሁ መልካም ቆይታ።

እኚህ እናት ከተወለዱባት ሰላ ድንጋይ ከወላጆቻቸው ጋር መጥተው አዲስ አበባ ነበር ያደጉት። አዲስ አበባ የወጣትነታቸው ጊዜ ሳያበቃ በወግ ተድረው ተኩለው እንደነበር ያስታውሳሉ። አግብተው ከትዳራቸው ሁለት ሴቶችና ሁለት ወንዶች ልጆችን አግኝተው በፍቅር በደስታ ይኖሩ ነበር። ደስታውና ፍቅሩም ባለቤታቸው በሞት እስከተለዩቸው ጊዜ ድረስ ቀጥሎ እንደነበር ያስታውሳሉ።

መልካም ሚስትና እናት ሆነው ባላቸው የሚያመጡትን ገንዘብ በጎተራ አካባቢ አርባ ሰባት የሚባል ሰፈር በምትገኘው አነስተኛ የቀበሌ ቤት እያብቃቁ ደስታና ፍቅር ይሞሉበት ነበር። ያገኙትን በሙሉ ልጆቻቸውን ለማሳደግ አንድም ነገር ሳይጎል ለማኖር ሲሉ ያወጡ ስለነበር ምንም ተቀማጭ ገቢ አልነበራቸውም።

ዛሬ የገዙት አስቤዛ ካለቀ ስለነገው ብዙም የማይገዳቸው እለት እለቱን የሚኖሩት እነ ወይዘሮ ወርቅነሽ የሚቀጥለውን ወር ቀለብ ለመግዛት የሚያስችል ሰባራ ሳንቲም እንኳን ሳይኖራቸው ነበር የትዳር አጋራቸው የልጆቻቸው አባት በሁለት በሶስት ቀን ህመም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት። የለቅሶው ሥርዓት አልቆ ሁሉም ሰው በየቤቱ ሲከተት ለልጆቻቸው የሚያቀምሱት ነገር ከእጃቸው ማጣት ጀመሩ።

የልጆቻቸው አባት ከሞቱ በኋላ ዓመት እንኳን ሳይቆይ ችግር ጓዙን ጠቅልሎ ቤታቸው ገባ። በዚህ ሲሉት በዚያ ሲቀደድ፤ ይሄንን ሲደፍኑት ያኛው ሲያፈስ፤ በሰቀቀን ሲንገዳገዱ ቆይተው ለልጆቻቸው መሆን እንደማይችሉ ሲያወቁት ቢያንስ ትንንሾቹ በረሃብ ከማለቃችን በፊት ለዘር ይትረፉ በማለት ወንድ ልጆቻቸውን በጉዲፈቻ አሜሪካን ሀገር ለሚኖሩ ነጮች ይሰጣሉ።

“ልጆቼ ዓይኔ እያየ እንዳይሞቱብኝ ስል ትልልቆቹን አጠገቤ አስቀርቼ የአምስትና የሰባት ዓመት እድሜ ያላቸውን ልጆቼን ለፈረንጆቹ ሰጠሁ። ያኔ በልጆቹ ናፍቆት የተሰቃየሁትን ሰቃይ መቼም አልረሳውም” የሚሉት ወይዘሮ ወርቅነሽ ችግር የአብራካቸውን ክፋዮች አሳልፈው እንዲሰጡ ካደረጋቸው በኋላ ጤና ማጣታቸውን ይናገራሉ።

ወንዶቹን ለጉዲፈቻ ከሰጡ በኋላ ሁለቱን ሴት ልጆች በትግል ሊያሳድጉ ቢሞክሩም እንዲህ በቀላሉ የሚገፋ አልሆነም፤ ልጆቹም ደጅ ማየት ለመዱ።

አሁን ላይ ውጭ ካሉት ልጆቻቸው ጋር በማህበራዊ መገናኛ ብዙሃን ቢገናኙም በቋንቋ ምክንያት የልባቸውን ተነጋግረው ስላልተግባቡ ውስጥ ውስጣቸውን ይበላቸዋል። ልጆቻቸው በሕይወት እንዳሉ ማወቃቸው ግን እፎይታ እንደሰጣቸው ይናገራሉ።

**ልጅቱ ተደራራቢ የጤና እክል ያለባት በመሆኗ እንደ ልጅ ሳትሮጥ አልጋ ላይ ቀረች። ልዩ ፍላጎት ያላት ከመሆኗም በላይ ቀኑን ሙሉ አንድ ወንበር ላይ ተቀምጣ የምትውልም መገላበጥ የሚቸግራት ልጅ ሆነች**

ከሴቶቹ ልጆቻቸው አንዷ አረብ ሀገር በስደት የምትኖር ሲሆን ብዙም ሊሳካላት አልቻለም። የሌላዋ ልጅ ታሪክ ደግሞ እንደሚከተለው ነው። ይህቺ ልጅ እኔና ወይዘሮ ወርቅነሽ እንድንገናኝ ምክንያት የሆነችና በትኩረት ለሴቶችና ለሕፃናት ማህበር የልዩ ፍላጎት ያላቸው ሕፃናት ማዕከል ውስጥ በመረዳት ላይ ያለች ልጅ ናት።

ከአራቱ ልጆቻቸው መካከል አንዷ ታማሚ የሆነች በወጣችበት ውላ የምታድር ትሆናለች። በዚህ መካከል አንዲት ሴት ልጅ የወለደችው የወይዘሮ ወርቅነሽ ልጅ ሕፃኗን ለማሳደግ ምንም ፍላጎት ሳይኖራት እሳቸው ላይ ትታ ሄደች። “ለነገሩ ለሳድጋት ብትልም ህመሙ እያሰቃያት ልጅቷ ከገጠማት ጉዳት በላይ ታከብድባት ነበር” የሚሉት ወይዘሮ ወርቅነሽ ይህችን ስጦታዬ የሚሏትን ልጅ ተቀብለው ማሳደግ ጀመሩ።

ልጅቱ ተደራራቢ የጤና እክል ያለባት በመሆኗ እንደ ልጅ ሳትሮጥ አልጋ ላይ ቀረች። ልዩ ፍላጎት ያላት ከመሆኗም በላይ ቀኑን ሙሉ አንድ ወንበር ላይ ተቀምጣ የምትውልም መገላበጥ የሚቸግራት ልጅ ሆነች።

ልዩ ፍላጎት ያላቸው ሕፃናት ከሌሎች ልጆች የበለጠ ፍቅር እንደሚፈለጉ ሁሉ የወይዘሮ ወርቅነሽም ልጅ አንዳንድ ቃላት በማውጣትና በማቀፍ ፍቅሯን የምትገልፅ አሳዛኝ ልጅ መሆኗን አያትዋ ይናገራሉ።

እንደ ወይዘሮ ወርቅነሽ ገለፃ ሕፃናቱን የያዙ ወላጆች ላይ ማህበረሰቡ ውስጥ ያለው አመለካከት አሉታዊ ነው። ሰው ልጆቹ በእርግማን ነው የተገኙት የሚለውን አስተሳሰብ በመቀየር ለእነዚህ ድርብርብ የጤና ችግር ላለቸው ሕፃናት ፍቅር መስጠት ይገባል ይላሉ።

የወይዘሮ ወርቅነሽ የልጅ ልጅ ባላት ልዩ ፍላጎት ችግር ምክንያት ያልተለመዱ ባህሪያት ቢኖራትም እንደ ልቧ አለመንቀሳቀሷ ግን ከሁሉ በላይ የሚያስከፋቸው መሆኑን ይናገራሉ። የቤቴ ድምቀት ናት የሚሏትን የልጃቸውን ልጅ የምታያሳየው ሰውን የመውደድና የፍቅር ስሜት ለመዋደድ ምንም ዓይነት የጤና ችግር እንደማይገድብ ጥሩ ማሳያ ናት ይላሉ።

የወይዘሮ ወርቅነሽ የልጅ ልጅ የተሻለ ሁኔታ ላይ እንድትሆን ሕክምና እንደሚያስፈልጋት የሚናገሩት አያቷ “ የተሻለ ሕክምና አግኝታ መንቀሳቀስ ብትችል በእድሜ ማምሻ ላይ ያገኘኋትን በረከቴን ሳልሞት እራሷን ችላ ብመለከት ምኞቴ ነው። ልጅቷ የተሻለ እንክብካቤ ብታገኝ በሕክምና ብትረዳ ለውጥ ታመጣለች ብዬ አምናለሁ” የሚሉት እኚህ ሴት ልጅቷን የሚያሳክምላቸው ሰው እንደሚፈልጉ በእንባ ተማፅነዋል።

ወይዘሮ ወርቅነሽ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ሁሉም ወረዳዎች ውስጥ የሚንቀሳቀሰው ድርጅት ውስጥ የተወሰነ ድጋፍ እያገኙ እንደሆነ ይናገራሉ። ማህበሩ እኔና እሳቸው በተገናኘንበት የፋሲካን በዓልን አስመልክቶ በተዘጋጀው ዝግጅትም ለወይዘሮ ወርቄና ተደራራቢ የጤና ችግር ላለባቸው ከሁለት መቶ ህምሳ እናቶችና ውስጥ መቶ ሰባ አምስት ለሚሆኑ ሕፃናት እናቶቻቸው የዱቄት እና የዘይት ዶሮና እንቁላል 1ሺ500 የኪስ ገንዘብ ስጦታን አበርክቷል።

ትኩረት ለሴቶችና ለሕፃናት ማህበር መስራችና ዳይሬክተር ወይዘሮ አሳየች ይርጋ እንደተናገሩት ለስጦታው የሚሆን ገቢ የተገኘው ከተለያዩ ለጋሾች በቀረበ ጥያቄ ሲሆን ፤ በተጨማሪም የኦቲዝም ቀንን አስመልክቶ በተዘጋጀ የማስ ስፖርት ላይ ነው። በዚህ ስፖርት እንቅስቃሴ ላይ ማህበሩ ሰፊ የሚዲያ ሽፋን በማግኘቱ በርካታ ሰዎች በራሳቸው ዶሮ እንቁላልና ገንዘብ አበርክተዋል። ሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ በየዓመቱ ለአዲስ ዓመትና ለፋሲካ በዓላት ድጋፍ ስለሚያደርግ ለእናቶቹ የሚሰጠው ስጦታ ዓይነቱ በዛ እንዲል ሆኗል።

በዚህኛው በዓል ለመቶ ሰባ አምስት እናቶችና ልጆቻቸው ድጋፍ የሚደረግበት ምክንያት ከወር በፊት በነበረው የሙስሊም ማህበረሰብ በዓል ላይም ተመሳሳይ ድጋፍ በመደረጉ የተነሳ መሆኑን ሲስተር አሳየች ትናገራለች።

በአኬኸርያ መንደር ውስጥ ተደራራቢ የጤና ችግር ያለባቸው 18 ሕጻናት የሚገኙ ሲሆን ለእነዚህ ሕፃናት በጤና፣ በምግብ፣ በመጠለያ፣ በትምህርት እና የሥነ-ልቦና አገልግሎት እየተሰጠ የሚገኝ ሲሆን ለጋሾች የሚሰጡት የዓመት በዓል መዋያም ለተረጂዎቹ እንደሚሰጥ ተናግራለች።

ተደራራቢ የጤና ችግር ያለባቸውን ልጆች እጅግ አስቸጋሪዎች በመሆናቸው እነሱን ይዘው



ወይዘሮ ወርቅነሽ አሰፋ

ያለ ምንም ገቢ የሚኖሩት እናቶች መደገፍ የሁሉም ማህበረሰብ ግዴታ ሊሆን ይገባል የምትለው ወ/ሮ አሳየች ሕፃናቱ በማህበረሰቡ ውስጥ ሲገለሉ የኖሩ ሲሆን የሚገባቸውን ድጋፍ እና እንክብካቤ ማግኘት ሳይችሉ ኖረዋል። በዚህም ምክንያት ለተለያዩ የጤና፣ የኢኮኖሚ እንዲሁም የሥነ ልቦና ቀውስ ተጋላጭ ሆነዋል። ይህንን ለመቅረፍ ደግሞ ሁሉም ማህበረሰብ የበኩሉን ሊወጣ ይገባል ትላለች።

ትኩረት ለሴቶችና ለሕፃናት ማህበር ተደራራቢ የጤና ችግር ያለባቸውን ሕፃናት ማቆያ፣ ትምህርት ቤት ፣ ሆስፒታል እና ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ኦሮሚያ ክልል፣ ሸገር ከተማ፣ ፉሪ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ 1 ልዩ አገልግሎት እየሰጠ የሚገኝ ሲሆን ላለፉት 17 ዓመታት አዲስ አበባን ጨምሮ በአራት ማዕከላት በማህበረሰብ ውስጥ ወላጆቻቸውን ላጡና ለችግር የተጋለጡ ሕፃናት ፣ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሴቶች ድጋፍና እንክብካቤ እንዲሁም የኤች አይ ቪ ስርጭት ለመቀነስ ወደ 12 ሺህ ገደማ የህብረተሰብ አካላትን ተጠቃሚ እያደረገ መቆየቱን ለቀጣይ ታብራራለች።

ጠጋ ብሎ ስለችግራቸው ለጠየቃቸውም ሀዘናቸው ተጋብቶበት ልብ የሚነካ አሳዛኝ ስሜት ውስጥ ይገባል። በጥቂት ደጋጎች ድጋፍ እነዚህ አሳዛኝ ሕፃናት ድጋፍ እያገኙ ቢሆንም ድጋፉ ግን በቂ ባለመሆኑ ሁሉም ዜጋ የተቻለውን ሊያበረክት ይገባል። ህምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክሙ ለህምሳ ሰው ጌጡ ነውና ይህንን የማህበረሰብ ችግር በመረዳት ሁሉም ማህበራዊ ኃላፊነቱን መወጣት ይጠበቅበታል።

በየቤቱም ልክ እንደ ወይዘሮ ወርቅነሽ ዓይነት በልጆቻቸው ምክንያት ቤት ተዘግቶባቸው በሀዘንና በችግር የሚደቆሱትን እናቶች መመልከት የማህበረሰቡ ኃላፊነት ነው። ልጆቹ የምድር ስጦታዎች እንደመሆናቸው ሁሉም ሰው የየራሱን ጠጠር በመጣል የችግሩን ስፋት ሊቀንስ ይገባል በማለት የዛሬውን ጽሑፍ ቋጭተናል። ቸር ይግጠመን።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

አዲስ ዘመንን በትውስታ፤ ትዝታን ይዞ 50 ዓመታትን ወደኋላ...ከሀገር ውስጥ እስከ ባህርማዶ፤ የዓለማችንን የኋላ ታሪክና አስገራሚ እውነታዎችን እናገኝበታለን። በዚያን ጊዜ... የመብራት ኃይሉ ሠራተኛ፤ ከመጠጥ ቤት አሊያም ከአሳቻ ስፍራ ሳይሆን፤ ከዚያው ከመሥሪያ ቤቱ ሠገነት ላይ በባልደረባው አምስት ጥይቶችን አርከፍክፎ፤ የገዛ ግንባሩንም በጥይት በመንደል፤ ሁለቱም ጎን ለጎን ተዘርረዋል። በጩቤ አስፈራርቶ፤ አህያ የሚሰርቀው ሌባስ፤ ምን ዓይነቱ ሌባ ይሆን...የ80 ዓመቷ አዛውንት፤ ለድፍን ስምንት ዓመታት የጠፉችውን ድመታቸውን በመፈለግ፤ በሬዲዮና በጋዜጣ ሳይቀር አፋልጉኝ እያሉ ሀብት ንብረታቸውን አንጠፍጥፈውላታል። አስገራሚውን ታሪክ፤ ከጥቂት የጳውሎስ ኞኞ ደብዳቤዎች ጋር ትውስታን እናጭርባቸው።

### የመብራት ኃይል ሠራተኛ ጓደኛውንና ራሱን ገደለ

አዲስ አበባ ኢ.ዜ.አ፡- ካሳዬ ኃይሌ የተባለ የኤሌክትሪክ መብራትና ኃይል ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት ባልደረባ፤ ሰይድ አብደላ የተባለውን የዚሁ መሥሪያ ቤት ሠራተኛ ትናንት ከቀኑ 6 ሰዓት ላይ ምክንያቱ ባልታወቀ ሁናቴ በሽጉጥ ተኩሶ ከገደለው በኋላ፤ ራሱንም በያዘው ሽጉጥ ተኩሶ የገደለ መሆኑን ከፖሊስ የተገኘው ዜና ገለጠ።

ገዳይ ካሳዬ ኃይሌ ዕድሜው 30 ዓመት፤ ሟች ሰይድ አብደላ ዕድሜው 28 ዓመት በደጎል አደባባይ አጠገብ የኤሌክትሪክ መብራትና ኃይል ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት በዋጋ ትንተና ክፍል ይሠሩ ነበር። የሁለቱም አስከሬኖች ከመሥሪያ ቤቱ 3ኛ ፎቅ ላይ ተዘርረው መገኘታቸውን የሁለተኛ ፖሊስ ጣቢያ ቃል አቀባይ አስታውቋል።

የፖሊስ ጣቢያው ምርመራ ማረጋገጫ ክፍል፤ ካሳዬ ኃይሌ የተባለው ቁጥር 96 ፖ 218 በሆነ አነስተኛ የአሜሪካ ኮልት ሽጉጥ 5 ጥይት ተኩሶ ሰይድ አብደላን ከግራ ጆሮው አጠገብና ከቀኝ እግሩ ባቱ ላይ በመምታት የገደለው መሆኑንና አምስቱም የተተኮሱት ጥይቶች ቀለህ፤ በዚያው በበረንዳው ላይ መገኘቱን አመልክቷል።

እንዲሁም ገዳዩ በድጋሚ አምስት ጥይት አጉርሶ በአንድ ጥይት ራሱን በገዛ እጁ ከግንባሩ ላይ መትቶ የገደለ መሆኑንና የቀሩት 4ቱ ጥይቶች ከነሽጉጡ መገኘታቸውንና የሁለቱም ሬሳ በወለሉ ላይ እንዳለ የአዲስ አበባ ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ክፍል ቴክኒካዊ ማስረጃዎችን ከወሰደ በኋላ አስከሬኑን ለምርመራ ወደ ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል የተላከ መሆኑን ገልጧል።

( አዲስ ዘመን መጋቢት 6 ቀን 1966ዓ.ም)

### አህያ የሰረቀው 3 ዓመት ተፈረደበት

አህያ ከታሰረበት ፈትቶ የሰረቀው የሱፍ ሐጂ አብዱላሂ፤ በ3 ዓመት እስራት እንዲቀጣ የሐረር ከፍተኛው ፍርድ ቤት ከትናንት በስቲያ በዋለው ችሎት ፈረደ።

የሱፍ ሐጂ አብዱላሂ ይህንን ወንጀል የፈጸመው፤ በድሬዳዋ ከተማ ባለፈው ነሐሴ 15 ቀን 62ዓ.ም ነው። ባለንብረቱ በዚያው ዕለት የተወሰደውን አህያ ከነኮርቻው ከአንድ ዛፍ ጥግ አስሮ ውሀ ለማመላለስ ወረፋ ይጠባበቅ እንደነበር አንድ የፍርድ ቤቱ ቃል አቀባይ ገልጧል።

ተከሳሹ አህያውን ከታሰረበት ሥፍራ ፈትቶ በወሰደበት ወቅት፤ ባለቤቱ ተከታትሎ ደርሶበት ነበር። ነገር ግን ተከሳሹ ባለቤቱን በጩቤ አስፈራርቶ አህያዋን በኃይል መውሰዱ በሕግ ምስክሮች ተረጋግጦበታል። በዚህም ምክንያት ፍርድ ቤቱ በየሱፍ ሐጂ አብዱላሂ ላይ የ3 ዓመት እስራት በይኗል። አህያው 65 ብር እንደሚያወጣ የተገመተ መሆኑንም ቃል አቀባዩ አስረድቷል።

(አዲስ ዘመን ነሐሴ 24 ቀን 1962ዓ.ም)

### ብታምኑም ባታምኑም የ80 ዓመቷ አዛውንት ድመታቸውን ፍለጋ ተሰደዱ

ሚስስ ግላዲስ ሞርቶን የተባሉ የ80 ዓመት አዛውንት አብራቸው የኖረች እንደልጅ ያሳደጓት ድመት ከስምንት ዓመት በፊት ጠፍታባቸው በሬዲዮ፤ በጋዜጣ ማሳወጅና ለአፈላላጊ ወሮታ ከ5ሺህ ብር በላይ ወጪ አድርገዋል።

አሁንም ተስፋ ሳይቆርጡ የመጨረሻውን ፍለጋ ለማድረግ ቤታቸውን ቆላልፈው ከወጡ 15 ቀን ሆኗቸዋል። እስካሁንም ወደቤታቸው አልተመለሱም።

ሰው አስገድዶ ወስዶብኝ መሆን አለበት እንጂ፤ ድመቴ እኔንና ቤቷን እንደምትወድ አውቃለሁ። አሁንም ቢሆን፤ ልታገኘኝ የምትችልበት ዘዴ ጠፍቷት ይሆናል እንጂ፤ በልቧ ሳታስበኝ አትቀርም በማለት ሊያጽናናቸው ለመጣ እንግዳ ሁሉ አዛውንቷ የሚያዋዩት ይህንኑ ነው።

ፑ የተባለችው የሚስስ ሞርቶን ድመት የጠፋችው እ.ኤ.አ. በ1963ዓ.ም በሰኔ ወር ነው።

ሚስስ ሞርቶን በነዚህ ዘመናት ሁሉ ፑን ለማግኘት ያልወሰዱት ርምጃ ያላዩት ሰው የለም። ጧት ጧት ሁል ጊዜ በየመንደሩ እየዞሩ ድንገት ድምጼን ሰምታ ትመጣ ይሆናል በማለት "ፑ" እያሉ ሲጣሩ ይውሉ ነበር።

ሚስስ ሞርቶን ድመታቸው ከተለየቻቸው ጀምሮ ኑሯቸውን አስተሳሰባቸውንና ጠቅላላ ሁኔታቸውን ያየ ሁሉ ከንፈሩን የማይመጥ የለም።

ድመታቸውን ለመፈለግ በማለዳ እየተነሡ ፍለጋና ጥሪ በማድረግ ጎረቤቱን ማስመረራቸው ታውቋል። የእኚህኑ አዛውንት ጭንቀት የተመለከቱ ብዙ ሰዎች የፑን መሰል ድመት እያመጡ ተገኘች እያሉ ቢደልሏቸውም አልመስል እያላቸው አልተቀበሉም።

ድመታቸውና እርሳቸው አብረው በሚኖሩበት ጊዜ የነበራቸውን ደስታና ኑሮ ሲያስታውሱ ብቻቸውን ከማልቀሳቸውም ሌላ፤ ለሰው ሲናገሩም የሰማውንም ሰው ሆድ ያባባሉ።

"ከእንግዲህ ወዲህ እኔና ድመቴ ወጣት አይደለንም፤ ያለኝንም ሀብት በማፈላለጊያ ጨርሻለሁ፤ የሕይወቴም ጊዜ እያለቀ መሔዱ ነውና በሕይወት እንዳለሁ እርሷን ላገኘልኝ ሰው ያለኝን ሀብት ለመስጠት ቃል ገብቻለሁ" በማለት በሬዲዮና በጋዜጣ አሳውጀው አሁንም በፍለጋ ላይ ናቸው።

(አዲስ ዘመን መስከረም 13 ቀን 1964ዓ.ም)

### ከእርስዎ ለርስዎ

_አዘጋጅ ጳውሎስ ኞኞ

*ጸጉሬ ባፈገፈገ ቁጥር የደመና ግላጭ ጸሐይን መቋቋም አቅቶኛል። ምን ይሻለኛል?

_ የአንበሳ ጎፍር ለጥፍበት እንዳልልህ ወደ ኬንያ መሻገር ሊኖርብህ ነው። የእኛዎቹ እንደሆን በአደንና በስደት አልቀዋል።

*አቶ ጌታቸው ደስታ ሀሙስ ማታ በሚያዘጋጀው የእንግሊዘኛ ዘፈን ፕሮግራም አብዶ እየሠራ አስቸግሮናል። ይኸውም ያንኑ ዘፈን እየደጋገመ በየሳምንቱ ያሰማናል።

ቴውድሮስ ዓለማየሁ(ከገለምሶ)

-ይሉሃል!።

(አዲስ ዘመን ታህሳስ 20 ቀን 1965ዓ.ም)

# ዓለም አቀፍ

## ከ150 ዓመታት በፊት ከጋና የተሰረቁ ቅርሶች ለእይታ በቁ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



ከጋናው የአሳንቲ ሥርወ መንግሥት በእንግሊዝ ቅኝ ገዢዎች የተመዘበሩ ቅርሶች ከ150 ዓመታት በኋላ ለዕይታ በቅተዋል።

የአሳንቲ መዲና በሆነው ኩማሲ በሚገኘው ማናህያ ቤተ መንግሥት ሙዝየም ውስጥ 32 ቅርሶች ለዕይታ ቀርበዋል።

"ዛሬ ቀኑ የአሳንቲ ነው። የጥቁር አፍሪካ ቀን ነው። የምንጋራው መንፈስ ተመልሷል" ሲሉ የአሳንቲ ንጉሥ ኦቱምፎ ኦሲ ቱቱ ተናግረዋል። እነዚህ ቅርሶች ለሦስት ዓመታት ነው በውሰት ለጋና የተሰጡት።

የእንግሊዞቹ ሙዝየሞች 'ዘ ቪክቶሪያ ኤንድ አልበርት ሙዝየም' እና 'ብሪትሽ ሙዝየም' ከአሳንቴ ንጉሥ ጋር ባደረጉት ስምምነት ነው ውሰቱ የተከናወነው። በዚህ ስምምነት ውስጥ የጋና መንግሥት የለበትም።

አሳንቴኔ በመባል የሚጠሩት የአሳንቴ ንጉሥ የባህላዊ አስተዳደር ተምሳሌት ናቸው።

ቅርሶቹ የንጉሡ አያት ቅድመ አያቶች መንፈስ አብሯቸው እንዳለ ይታመናል። ይህ ሥርወ ግዛት አሁን የጋና አስተዳደር አካል ነው።

የአሳንቲ አባል የሆነው ሄነሪ አማንክዊታ "ክብራችን ተመልሷል" ሲል ስሜቱን ይገልጻል። ከሁለቱ ሙዝየሞች 17 እና 15 ቅርሶች በውሰት ተሰጥተዋል። በማኅበረሰቡ ዘንድ የቅርሶቹ መመለስ ደስታን ፈጥሯል።

ከእነዚህ ቅርሶች መካከል የተወሰኑት የተሰረቁት በአንግሎ-አሻንቲ ጦርነት በ19ኛው ክፍለ ዘመን ነው። ሌሎቹ ደግሞ እአአ በ1817 ለእንግሊዝ ዲፕሎማት የተሰጡ ናቸው።

የቪክቶሪያና አልበርት ሙዝየም ዳይሬክተር ከዶ/ር ትሪሳም ሁንት፣ "እነዚህ ቅርሶች በኛ ይዞታ ሥር የመጡበትን አስቀያሚ ታሪክ እንገነዘባለን። የኢምፔሪያሊዝምና ቅኝ ግዛት ጠባሳ አለባቸው" ብለዋል።

ከተመለሱት ቅርሶች መካከል 'መፖኮፖመሶ' የተባለ ሰይፍ ይገኝበታል። በአሳንቲ ሕዝብ ትልቅ ዋጋ የሚሰጠው ነው።

የጎሳ መሪዎች በዓለ ሲመት ላይ ቃለ መሀላ የሚፈጸምበት ነው።

የነገሥታት ታሪክ ምሁር አሲ-ቦንሱ ሳፎ-ካታና ለቢቢሲ እንደገለጹት፣ እነዚህ ቅርሶች ከአሳንቲ ሲወሰዱ የሕዝቡም ልብ፣ ቀልብና ማንነት አብሮ ተሰርቋል። የቅርሶቹ መመለስ አነጋጋሪና ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጠውም ነው።

በዩናይትድ ኪንግደም ሕግ መሠረት፣ ሁለቱ ሙዝየሞች ውዝግብ የሚነሳባቸው ቅርሶችን በዘላቂነት መመለስ አይችሉም።

ቅርሶችን በውሰት መስጠት ወደ ባለቤት ሀገራቸው የመመለስ ሂደት ተደርጎ ነው የሚወሰደው።

አንዳንድ ሀገራት ግን 'ውሰት' የሚል አገላለጽ ዩኬ የቅርሶቹ ባለቤት እንደሆነች ትርጓሜ የሚሰጥ ነው ብለው ይከራከራሉ ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።

## በእስራኤል የሚገኘው የአልጀዚራ ጣቢያ ተዘጋ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በእስራኤል የሚገኘው የአልጀዚራ ቴሌቪዥን ጣቢያ መዘጋቱ ተዘገበ፡፡ "ጣቢያው የተዘጋው የሐማስ አፈ ቀላጤ ሆኗል'' በሚል ነው። ጠቅላይ ሚኒስትር ናታንያሁ "የእስራኤል ካቢኔ ጣቢያው እንዲዘጋ ወስኗል" ብለዋል። ይህን ተከትሎ ፖሊስ በጣቢያው ቢሮ ኢየሩሳሌም፣ አምባሳደር ሆቴል ብርበራ አድርጓል።

እስራኤል "አልጀዚራ ለብሔራዊ ደኅንነቴ ሥጋት ነው" ማለቷን ጣቢያው፣ "ቀሽም ነገር ግን አደገኛ ውሸት" ሲል አጣጥሎታል። ጣቢያው በሕግ መብቱን እንደሚያስከብርም ዝቷል።

የእስራኤል የኮሚኒኬሽን ሚኒስትር ሽሎሞ ካርሂ በድንገተኛ ወረራው አንዳንድ ቁሳቁሶች ተወስደዋል ብለዋል። በዚሁ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት የኤክስ ገጽ በተለጠፈ ተንቀሳቃሽ ምሥል ፖሊሶች ወደ ሆቴሉ ገብተው ሲበረብሩ ያሳያል።

የቢቢሲ ጋዜጠኞች ወደ ሥፍራው አቅንተው የነበረ ቢሆንም ወደ ውስጥ እንዳይገቡ፣ ክስተቱንም እንዳይቀርጹ ተከልክለዋል ተብሏል።

ሮይተርስ እንደዘገበው የእስራኤል ሳተላይት አገልግሎት አልጀዚራ ይታይበት በነበረ ምሥል አሁን የጽሑፍ መልእክት ብቻ እየታየ ይገኛል፤ መልእክቱም "መንግሥት በወሰነው መሠረት በእስራኤል የአልጀዚራ ሥርጭት እንዲቆም ተደርጓል" የሚል ነው።

አልጀዚራ በሳተላይት ይታገድ እንጂ አሁንም በእስራኤል በፌስቡክ እየታየ ነው። የሰብአዊ መብት ድርጅቶች መንግሥት አልጀዚራን ለመስጋት መወሰኑን አውግዘዋል።

የሲቪል መብቶች ኅብረት በእስራኤል ድርጊቱን ከኮነነ በኋላ ለሀገሪቱ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔውን እንዲቀለብስ ጥያቄ ማቅረቡን ተናግሯል።

ይህ የእስራኤል የሰብአዊ መብት ኅብረት እንደሚለው አልጀዚራ የሐማስ ድምጽ ነው የሚለው ክስ "ውሃ አያነሳም።''

አልጀዚራ እንዲዘጋ የተወሰነው በብሔራዊ ስጋት ምክንያት ሳይሆን የፖለቲካ ዉሳኔ ስለሆነ ነው፤ ድምጽን ለማፈን የሚደረግ ሙከራ ነው ብሏል ኅብረቱ።

የውጭ ሚዲያዎች ማኅበር በእስራኤል በተመሳሳይ የአልጀዚራን መዘጋት "አሳሳቢ" ሲል ገልጾታል።

የጋዜጠኞች መብት ተቆርቋሪው ሲፒጄ ፕሮግራም ዳይሬክተር ካርሎስ ማርቲኔዝ ዴ ላ ሰርና የእስራኤል መንግሥት በተለይ በጦርነት ጊዜ የዓለም አቀፍ ሚዲያዎችን በነጻነት እንዲሠሩ ማድረግ ሲገባው በተቃራኒው አልጀዚራን መዝጋቱ አሳሳቢ ነው ብለዋል።

የተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብት ቢሮም የእስራኤል መንግሥት ውሳኔውን በድጋሚ እንዲያጤነው ጠይቋል።

የውጭ ሚዲያዎች ጋዛ እንዲገቡ አይፈቀድላቸውም። ብቸኛው በጋዛ ሪፖርተሮች የነበሩት አልጀዚራ ነበር። የእስራኤል ባለሥልጣናት ለዓመታት አልጀዚራን ''ጸረ-እስራኤል'' በሚል ሲከሱ ቆይተዋል። ይህ ክሳቸው በተለይ ሐማስ መብረቃዊ ጥቃት ፈጽሞ 1200 ሰዎችን ከገደለ በኋላ ተጠናክሮ ቀጥሏል። ይህን የሐማስ ጥቃት ተከትሎ 34ሺህ 683 ፍልስጤማዊያን ተገድለዋል፤ 70ሺህ 18 ሰዎች ደግሞ ቆስለዋል። በሐማስ የሚመራው የጤና ሚኒስትር እንደሚለው ከሟቾቹ መካከል የሚበዙት ሴቶችና ሕጻናት ናቸው።

የአልጀዚራ ዋና መሥሪያ ቤት የሚገኘው ኳታር ሲሆን ይቺ ሀገር በሐማስና በእስራኤል መካከል ቁልፍ አሸማጋይ እንደሆነች ይታወቃል። ከዚህ ቀደም ኳታር ሁለቱን ተዋጊዎች አሸማግላ ጊዜያዊ የተኩስ አቁም ተደርጎ፣ 105 እስራኤላዊ ታጋቾች መለቀቃቸው አይዘነጋም። አልጀዚራ እንደሚለው እስራኤል የጣቢያውን ጋዜጠኞች ሆን ብላ ገድላለች።

ከነዚህ መካከል መላ ቤተሰቡ የተገደለበት የአልጀዚራ የጋዛ ቢሮ ኃላፊ ዋ'ል አልደህዱህ የበኩር ልጅ ሐምዛ አል-ደህዱህ የተገደለበት ሁኔታ ይጠቀሳል። እስራኤል ይህን ክስ ታስተባብላለች።

አልጀዚራ በእስራኤል መዘጋቱን ተከትሎ ባወጣው መግለጫ "እስራኤል ነጻ ፕሬስን በማፈን የምትፈጽመውን ግድያ መሸፈን አትችልም። ከዚህ ቀደም ጋዜጠኞቻችንን በመግደልና በማሰር ልታቆመን እንዳልቻለችው ሁሉ አሁንም የጋዜጠኝነት ተግባራችንን አጠናክረን እንቀጥላለን።" ብሏል።

# ስፖርት





# በፕራግ ማራቶን ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች አሸንፈዋል

ዓለማየሁ ግዛው

በየዓመቱ በቼክ ሪፐብሊክ በሚካሄደው የፕራግ ማራቶን በሳምንቱ መጨረሻ ለ30ኛ ጊዜ ሲካሄድ ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ውድድሩን በድል አጠናቀዋል። ውድድሩ በሁለቱም ጾታዎች ከፍተኛ ፉክክር አስተናግዶ በወንዶች አትሌት ለሚ ብርሃኑ፣ በሴቶች ደግሞ አትሌት በዳቱ ሂርጳ አሸናፊዎች ሆነዋል።

በዚህ የውድድር መድረክ የኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ድል አንድ ብሎ የጀመረው ውድድሩ በጀመረበት እአአ በ1995 ነበር። የድሉ ባለቤትም አትሌት ቱሞ ቱርቦ ሲሆን፤ ዘንድሮ የተመዘገበውን ጨምሮ ኢትዮጵያዊያን በፕራግ ማራቶን ከአስር ጊዜ በላይ አሸናፊዎች ሆነዋል። ለመጨረሻ ጊዜ እአአ 2019 በወንዶች አትሌት ዳዊት ወልዴ ሲያሸንፍ፤ በሴቶች ወርቅነሽ ኢዴሴ ያለፈው ዓመት ባለድል መሆኗ የሚታወስ ነው።

ውድድሩ እአአ በ2020 እና በ2021 በኮቪድ 19 ወረርሽኝ መከሰት ምክንያት ከሁለት ዓመት መቋረጥ በኋላ ወደ ፉክክር ከተመለሰ ወዲህም ቢሆን ኢትዮጵያዊያን ሴት አትሌቶች በድል ጎዳና መጓዝ ችለዋል። ስምንት ሴት አትሌቶች በተሰለፉበት የአሁኑ መድረክ፣ በዳቱ ሂርጳ ያስመዘገበችው ውጤት በሴቶች የተገኘ ሶስተኛ ተከታታይ ድል ለመሆን ችሏል። እንደተለመደው ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ከኬንያዊያን ጋር ብርቱ ፉክክር ቢገጥማቸውም አትሌቷ ውድድሩን በድል ማጠናቀቅ ችላለች። በዳቱ ሂርጳ ኬንያዊቷን ዶርካስ ቱኢቶክን አስከትላ በመግባት ነው የበላይነቱን የያዘችው።

አትሌቷ ከዚህ ቀደም ባደረገቻቸው ትልልቅ የማራቶን ውድድሮች በተደጋጋሚ ድል መቀዳጀት የቻለች ሲሆን እአአ በ2018 በፍራንክፈርት ማራቶን 2፡21፡32 በሆነ ሰዓት



አትሌት ለሚ ብርሃኑ፤

በመግባት ሶስተኛ ደረጃን ስትይዝ፣ ያስመዘገበችው ሰዓትም የግሏ ምርጥ በመሆን ተይዞላታል። ከ5 ዓመታት በፊት በቻይናዋ ሻንጋይ ከተማ በተካሄደው ውድድር የተመዘገበው 1፡12፡11 የሆነ ሰዓት ደግሞ በግማሽ ማራቶን የገባችበት የግሏ ቀዳሚ ሰዓት መሆን ችሏል።

በርካታ አትሌቶች ለድሉ ተጠብቀው 26 አትሌቶች ደረጃ ሰንጠረዥ ውስጥ ገብተው ባጠናቀቁት የፕራጉ ፍክክር 2፡23፡41 ሰዓት በማስመዝገብ ውድድሯን በበላይነት አጠናቀለች። ብርቱ ተፎካካሪዋ የነበረችው ኬንያዊቷ አትሌት ዶርካስ ቱኢቶክን 2፡24፡50 በመግባት ሁለተኛ ደረጃን ይዛ አጠናቃለች። አትሌት ሸዋረግ አለነ ደግሞ 2፡27፡32 በሆነ ሰዓት ገብታ ሶስተኛ ደረጃን ይዛ ውድድሯን




አትሌት በዳቱ ሂርጳ

ፈጽማለች። ጽግነሽ መኮንን፣ አፈራ ጎድፋይ፣ ሙሉሃብት ጺጋ እና ዝናሽ ደበበ ከአራተኛ እስከ ሰባተኛ ያለውን ደረጃ በመያዝ የኢትዮጵያዊያኑን የበላይነት አስመስክረዋል። የአምናዋ የመድረኩ ባለድል አትሌት ወርቅነሽ ኢዴሳ 2፡20፡42 ሰዓት በማስመዝገብ ከኢትዮጵያዊያን የመድረኩ አሸናፊ አትሌቶች የተሻለውን ሰዓት ይዛ ትገኛለች።

በወንዶች መካከል በተካሄደው እልህ አስጨራሽ ፉክክር አትሌት ለሚ ብርሃኑ በበላይነት በማጠናቀቅ ውድድሩን ማሸነፍ ችሏል። አትሌቱ ከኬንያዊያን እና ከሌሎች ሀገራት አትሌቶች የገጠመውን ብርቱ ፉክክር በመርታት ኬንያዊያኑን በማስከተል በቀዳሚነት አሸንፏል። ውድድሩን ለማጠናቀቅም 2 ሰዓት ከ 08 ደቂቃ ከ 44 ሴኮንድ ፈጅቶበታል። አትሌቱ የመጀመርያውን የማራቶን ውድድሩን የሮጠው እአአ በ2014 ዙሪክ በተካሄደ ሩጫ ሲሆን 2፡10፡40 በመግባትም አሸናፊ ነበር። ከአንድ ዓመት በኋላም በዱባይ ማራቶን አስገራሚ ብቃት በማሳየት፣ ቀድሞ ዙሪክ ላይ አስመዝግቦ የነበረውን ሰዓት ከ 5 ደቂቃ በላይ በማሻሻል ማሸነፍ ችሎ ነበር። በብዙ የጎዳና ላይ ውድድሮች በመሳተፍና በማሸነፍ ብዙ ድሎችን ማቀዳጀት እንዲሁም ከፍተኛ ልምድን ማካበት ቻለው አትሌቱ የፕራግ ማራቶንም አንጸባራቂ ድሉን ቀጥሏል። በትልልቅ የዓለም የጎዳና ላይ ወድድሮች ያካበተው ልምድና የአሸናፊነት መንፈስ ፉክክሩን ተቋቁሞ ለድል እንዲበቃ አስችሎታል። አንጋፋውን የቦስተን ማራቶንን ጨምሮ በትልልቅ የጎዳና ውድድሮች በማሸነፍ ከዓለም ምርጥ 15 የረጅም ርቀት ሯጮች ተርታ ለመሰለፍ የቻለበት ወቅትም ነበር። 2 ሰዓት ከ 04 ደቂቃ ከ33 ሴኮንድ የማራቶን የግል ምርጥ ሰዓቱ ሲሆን 1 ሰዓት ከ 01 ደቂቃ ከ37 ሴኮንድ የግማሽ ማራቶን የግል ምርጥ ሰዓቱ ነው።

ይህንን ውድድር ሲያሸንፍም ከ2 ሰዓት ከ10 ደቂቃ በታች የተመዘገበ 7ኛውን ፈጣን ሰዓት መያዝ ችሏል። የእሱ ተፎካካሪ የነበረው ኬንያዊው አትሌት ኪፕሮኖ ኪፕኬሞኢ በ2 ደቂቃዎች ዘግይቶ በማግባት ሁለተኛ ደረጃን በመያዝ አጠናቋል። ኮነ ጀሹአ ከኬንያ 2፡10፡51 ሰዓትን አስመዝግቦ ሶስተኛ ደረጃ በመያዝ ውድድሩን ጨርሷል። 2019 አትሌት ዳዊት ወልዴ ሲያሸንፍ ያስመዘበው 2፡06፡18 ሰዓት በኢትዮጵያዊያን ወንድ አትሌቶች የተመዘገበ የቦታው ፈጣን ሰዓት በመሆን ተመዝግቧል።

በመድረኩ ከዚህ ቀደም በወንዶች አትሌት ቱሞ ቱርቦን ጨምሮ ዳሬሳ ጪሚሳ፣ ገብረጻዲቅ አብረሃና ዳዊት ወልዴ ድል ማድረግ ችለዋል። በሴቶች ላይላ አማን፣ ፍሬህይወት ዳዶ፣ የብርጓል መለሰ፣ በቀለች ጉደታ እና ወርቅነሽ ኢዴሳ ያሸነፉ ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች በመሆን ተመዝግበዋል።


## ማረሚያ

ሚያዝያ 9 ቀን 2016 ዓ.ም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ገጽ 25 በባለንብረቱ ስም ከማል ሱሌማን መሀመድ በወጣው የሊብሬ መጥፋት ማስታወቂያ የሞተር ቁጥር 2Db-A510820 የተባለው በስህተት ስለሆነ የሞተር ቁጥሩ 2KD-A81820 መሆኑን እንገልጻለን፡፡

## በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል

የባለንብረቱ ስም ሚራጅ ከማል የሠሌዳ ቁጥር 1-36592 ደ/ህ ተሽከርካሪ ባጃጅ የሻንሲ ቁጥር MD6M14PA8N4AC3070 ሞዴል NPR-66 የሞተር ቁጥር AK4AN41B8845 ከላይ የተጠቀሰው ተሽከርካሪ 1-36592 ደ/ህ ታርጋ ጠፋብኝ ብለው በቁጥር 1054/ጉዞፖ/15/42 በ22/8/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ታርጋ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍርድ ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ አመልካች ተለዋጭ ታርጋ የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት የጉራጌ ዞን ትራንስፖርት**
**መንገድ ልማት መምሪያ**

## ኦሮሚያ ክልል

ንብረትነቱ ኤሊያስ ዘገዬ አበበ ስም የተመዘገበ የሠሌዳ ቁጥር OR-01-11551 የሆነ ተሽከርካሪ ሠሌዳ የጠፋባቸው መሆኑን በመግለጽ ሌላ ምትክ ሠሌዳ እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል፡፡ በዚህ መሠረት ሠሌዳው ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት የያዘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ሪፖርት እንዲያደርግ፡፡

**በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት መስተዳደር ቢሾፍቱ ከተማ**
**ትራንስፖርት ባለሥልጣን**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

ይ/ባይ፡- ፌ/ጠ/ዐ/ህግ እና መ/ሰጪ ናትናኤል ሸዋረጋ ሞሻጋ መካከል ስላለው የኮንትሮባንድ ወንጀል ክስ ጉዳይ 07/09/2016 ዓ.ም ሲሆን ቀነ ቀጠሮ በ4፡00 ሰዓት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ወንጀል ምድብ 3ኛ ጉምሩክ ወንጀል ችሎት እንድትቀርቡ የማትቀርቡ ከሆነ ግን ክሱ በሌላችሁበት ታይቶ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑ አውቃችሁ በእለቱ እንድትቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት**

## ማስታወቂያ

የቅርንጫፋችን ደንበኛ የሆኑት አቶ ፈንታሁን አግድ እምሩ በቀን 24/05/2016 ዓ.ም የባንኩ የረጅም ጊዜ ደንበኞ መሆናቸውን ጠቅሰው በፋሲለደስ በቅርንጫፍ በተንቀሳቃሽ ሂሳብ ቁጥር 1000037467417 /currenet account /በመክፈት ሲጠቀሙ የነበረ መሆኑን አሳውቀውናል። በመሆኑም የተከፈተውን ሂሳብ T -24 በቅርንጫፋችን ለማየት ችለናል። ይሁን እንጂ ሲጠቀሙበት የነበረው ሂሳብ በቂ ስንቅ የሌለው ቼክ ለደንበኞቹ በመስጠት/insuffienent check /

| ቀን | የቸክ ቁጥር | የገንዘቡ መጠን |
|---|---|---|
| 1. 15/06/2006 E.C | BC5790111 | 25,000 |
| 2. 27/05/2007 E.C | BC5790116 | 80,000 |
| 3. 22/11/2008 EC | BC5790117 | 26,000 በድምር |

131,000 የገንዘብ መጠን ሂሳብ በደረሰኝ ቁጥር ACLK24055K2HMY ከሂሳብ ቁጥር 1000037469452 ብር 131,000 /አንድ መቶ ሰላሳ አንድ ሺህ ብር/ ብቻ በዝግ ሂሳብ ያስቀመጥን መሆኑን በአክብሮት እገልጻለን።

**የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፋሲለደስ ቅርንጫፍ**

## የተጨማሪ እሴት ታክስ እጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ ይመለከታል

አቶ መሀመድ አብዱ ኢብረሂም በክልላችን በጨው ስራ ዘርፍ የተሰማሩ እና በግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፡- 0067894097 በተጨማሪ እሴት ታክስ ቁጥር፡- 16372470803 የተመዘገቡ የክልላችን ግብር ከፋይ ሲሆኑ የተጨማሪ እሴት ታክስ ገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ከተራ ቁጥር 00001 እስከ 000050 ድረስ ደረሰኝ ያልተሰራበት ደረሰኝ በጦርነት ምክኒያት የጠፋ መሆኑን ገልጸውልናል፡፡ ስለዚህ ደረሰኙን ያገኘው ግለሰብ ወይም ድርጅት ወንጀል እንዳይሰራበት ማንኛውንም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው ታክስ ከፋይነት ለተመዘገበኩበት ለአፋር ክልል ገቢዎች ቢሮ ወይም በአቅራቢያው ለሚገኘው ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት እንዲያሳውቅ እና በግብር ታክስ አሰባሰብ ላይ ለሚደረገው ለመልካም ትብብር እንዲያደርጉ እንገልጻለን፡፡

**በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ቢሮ**